## ክፍል ሁለት(2)፡- የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው





# ምዕራፍ ሁለት(2)
# ግጭትና የግጭት ተጽዕኖ

## 1. የግጭት ምንነት

በባለትዳሮች መካከል ስለሚፈጠሩ ልዩ ልዩ የግጭት ዓይነቶች፣ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው ከማሰባችን በፊት በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባትና ግጭት ምንነት ከመረዳት መጀመር መልካም ነው። የግጭትን ምንነት መረዳት ትክክለኛ፣ የተለመደ እና አይቀሬ የሆነውን ግጭት፣ የግጭት መንስኤና የግጭትን ተጽዕኖ ለመለየትና በፍጥነት መፍትሔ ለማፈላለግ ይጠቅማል። ግጭት በሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ ሰዎችና አሳቦቻቸው መካከል የሚፈጠር የስምምነት መጥፋት ወይም የአለመግባባት ሂደት ነው። በትዳር ውስጥ የሚፈጠረውን ግጭት ምንነት በሚከተሉት ሃሳቦች አጠቃልለን መዳሰስ እንችላለን፡፡ በትዳር ውስጥ የሚፈጠር ግጭት ማለት፡-

### 1. አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ የሚደረግ ትግል

ግጭት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መስማማት ከመጥፋቱ የተነሳ በባለትዳሮች መካከል የሚከሰት ለማሸነፍ የሚደረግ ትግል ነው። በተለይ ከተጋቡ ብዙ ያልቆዩ ጥንዶች በአንደኛው ወይም በሁለቱም ወገን ማሸነፍ የሚል መንፈስ ብቻ ሲኖራቸው አሸናፊ የመሆን ትግልና አፍራሽ ፍክክር ይጀመራል፡፡ ይህ ሁኔታ በጊዜ የማይቃና ከሆነ ክስተቱ የትግሉን ማብቂያ ጊዜ የሚያራዝመው ሲሆን ግጭቱ የሚፈጥረውን ጉዳትና የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖም እንዲጨምር ያደርገዋል።

### 2. ተስማምተውና ተጣምረው እንዳይሄዱ ሊያደርግ የሚችል ክስተት

ግጭት ባለትዳሮች ተስማምተውና ተጣምረው እንዳይሄዱ በመካከላቸው የሚፈጠር ክስተት ነው። ግጭት የሃሳብን ልዩነት በአግባቡ ማስተናገድ ባለመቻል ምክንያት በአሳብ የአለመስማማትና የአለመግባባት ውጥረት የመፈጠር ሂደት ነው፡፡ የተፈጠረው ውጥረት ሁለቱ (ጥንዶቹ) ተስማምተውና ተግባብተው በትዳራቸው ጠንካራ ግንኙነት እንዳይኖራቸው፣ ጥምረታቸው እንዲላላና ብሎም ፍች ላይ እንዲደርስ ሊያደርግ የሚችል ክስተት ሊሆን ይችላል። ክስተቱ እንዲሁ በጋራ ሲኖሩ ሳይታሰብ በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠርና ደግሞም ታቅዶና ተቀነባብሮ ሊፈጠር የሚችልም ክስተት ነው።

### 3. ልዩነቶች የሚገለጡበትና የሚፈልጉትን ለማግኘት እርስ በእርስ እንዳይግባቡ የሚያደረግ ሂደት

ግጭት በባለትዳሮች መካከል ያሉ ልዩነቶች የሚገለጡበትና የሚፈልጉትን ለማግኘት እርስ በርሳቸው የማይግባቡበት ሂደት ነው። በአንድ ሰው ጾታ፣ አስተዳደግ፣ ልምምድ፣ ባህሪይና እሴቶች የተነሳ ከሌላ ሰው ጋር ሲነፃፀር ልዩነት ሊኖረው የግድ

ነው። ይህ ልዩነት ይበልጥ ሊገለጥና ሊታወቅ የሚችለው ደግሞ ብዙ ጊዜ አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል ነው። በባለትዳሮች መካከል ያለው ቅርበትና መተዋወቅ ከሌሎች ግንኙነቶች የበለጠና የጠነከረ ነው። በዚህ የጠነከረ ግንኙነት ውስጥ ለጊዜው ተደብቆ የነበረው ልዩነት መገለጥ ሲጀምር ግጭት ይፈጠራል። የሁለቱ ጥንዶች የየግልና የተለያዩ ፍላጎቶቻቸውን ለማግኘት መፈለግና ጥረት ማድረግ ደግሞ ይበልጥ ግጭቱን ጠንካራ ሊያደርገው ይችላል።

## 4. በማናቸውም የጋብቻ ዘመን ክልል ሊፈጠር የሚችል ክስተት

ግጭት በማናቸውም ጥንዶችና በየትኛውም የጋብቻ ዘመን ክልል ውስጥ ባሉ ባለ ትዳሮች መካከል ሊፈጠር የሚችል ክስተት ነው። በትዳር ዘመናችን በቀናት፣ በሳምንታት፣ በወራት፣ በዓመታትም ይሁን በደረስንበት የጋብቻ ዘመን የግጭት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ልዩነቶችና ፍላጎቶች መኖራቸው የማይቀር ነው። ተጋቢዎች በመካከላችን ግጭት ተፈጥሮ አያውቅም ሊፈጠርም አይችልም ብለው የሚያስቡ ከሆነ እስከ አሁን አብረው በትዳር ብዙ አልቆዩም ወይም እውነተኛውን የትዳር ሕይወት እስከዛሬ አልኖሩትም ማለት ነው። ለዚህን ያክል ዓመታት አብረን ቆይተናል ካሉም ደግሞ አብረው እየኖሩ አይተዋወቁም እንዲሁም አይነጋገሩም ነበር ለማለት ያስደፍራል። አብረን እየተነጋገርን ነው የምንኖረው ብለው የሚያስቡ ከሆነ እውነትን በመናገር ሳይሆን በግብዝነት ወይም ከሰው ጋር ሳይሆን ከሮቦት ጋር ነው እንዴ

**ባለትዳሮች ሆይ አለመግባባትና ግጭት በትዳራችን የለም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም!!**

የሚኖሩት? ሊያስብልባቸው ይችላል። ሰው ሁለትና ከዚያም በላይ ሁኖ አብሮ መኖር ሲጀምር አለመግባባትና ግጭት....አይቀሬነቱ የታወቀ ነው!!

## 5. በአግባብ ካልተቆጣጠሩት በየጊዜው እያደገ ሊመጣ የሚችል ባህርይ አለው

ግጭት መጠኑና ዓይነቱ በየጊዜው እያደገ ሊመጣና ሊለዋወጥ ይችላል። ከዚህ አኳያ በጥንቃቄና በብስለት ካልተያዙ ማንኛቸውም የሚያነጋግሩ ርዕሰ ጉዳዮች ወደ አለመግባባትና አለመስማማት ያድጋሉ ግልጥ የሆነ የአሳብ ልዩነትም ይፈጠራል፡፡ የተፈጠረው የአሳብ ልዩነት ደግሞ ወደ መሸናነፍ ትግል ይለወጣል። ጥንዶቹ በትግሉ ሂደት ውስጥ ለማሸነፍ ተግቶ መዋጋት አሊያም መሸሽ እንዲመርጡ ይገደዳሉ። ይህም ሁኔታ የግጭቱ መጠን እንዲያድግ ወይም የተለያየ ገጽታ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡[3]

[3] ከበደ በከሬ, <u>የትዳር ግጭት መፍቻ ስልቶች</u> : መካነ ኢየሱስ የምስራች ድምፅ ኅትመት መገናኛ ዘዴ ክፍል፡ አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ 1999 ዓ.ም ገጽ 78-83





## 6. ግጭት አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖ ያለው መሆኑ

በማንኛውም መንገድ ሰዎች ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ሁነው የሚኖሩ ከሆነ በተለይም ደግሞ በትዳር ግንኙነት አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል ግጭት የማይቀር ነው። አለመግባባት ብሎም ግጭት በግንኙነታችን መካከል ሲፈጠር ደግሞ አሉታዊ አሊያም አዎንታዊ ተጽዕኖ አምጥቶ ማለፉ አይቀሬ ነው። የግጭቱ ተጽዕኖ እንደ ጥንዶቹ ግጭት አፈታት ብስለት ይወሰናል። አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ስንል ምን ማለት ነው? ምንስ ሲፈጠር ነው አሉታዊ (ክፉ፣ መጥፎና አፍራሽ የሆነ) ተጽዕኖ ነው የምንለው? የሚለውን በማወቅ አፍራሽ የሆነው የግጭት ተጽዕኖ እየተፈጠረ ከሆነ ከጉዳቱ ለማምለጥና ወደ ፊትም በትዳራችን ቋሚ ቀውስ ፈጥሮ እንዳያልፍ ለመጠንቀቅ ይረዳን ዘንድ የሚከተሉትን ሁለት ሃሳቦች በማስተዋል ማየት ጠቃሚ ነው፡-

**አሉታዊ ተጽዕኖ (አፍራሽ የሆነ)** ግጭት በተለያየ ጊዜና በተለያየ መንስኤ በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠር ሐቅ ነው። ግጭት ከተከሰተ በኋላ ባግባቡ ካልተፈታ ብዙ ጊዜ በባለትዳሮች ግንኙነት ላይ እርስ በርሳቸው እንዳይቀራረቡ የጥላቻን ተጽዕኖ ፈጥሮ የመሄድ አስተዋጾ አለው። መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን የትዳር አጋሮቻችንን ሌሎችን ሰዎች መጥላት እንደሌለብን እንዲህ ሲል ያዘናል፡- *"... ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ በጨለማም ይመላለሳል"፣ "ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው" እና "እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው..."* በማለት ሰውን የመጥላት ስሜት ካለን በምን አይነት ሕይወት እንዳለንና ውጤቱም ምን እንደ ሆነ በማሳየት ያስጠንቅቀናል /1ኛዮሐ 2: 11፣ 3: 15፣ 4: 20/።

ግጭት የፈጠረው ክፉ የጥላቻ ተጽዕኖ ጥንዶችን አንዱ በሌላው ላይ ለበቀል እንዲነሳሱና ይበልጥ እንዲጎዳዱ ሊያደርግ ይችላል። በግጭት ወቅት ያልተግባባንበትና ለግጭት ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በመለየት በይቅርታ ነገሮቻችንን ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት ካላደረግን የይቅርታ ተቃራኒ የሆነውን በቀልን እንድንለማመድ ያደፋፍረናል። እንደ ክርስቲያን ባልና ሚስት ከመበቀል ይልቅ ክርስቶስ እኛን ይቅር ብሎ እንደ ተቀበለን እርስ በርሳችን ልንቀባበል እንደሚገባ ቃሉ ያዘናል /ኤፌ 4: 32፣ቆላ 3: 13/።

ሌላው የግጭት አሉታዊ ተጽዕኖ ሁልጊዜ የእኔ አሳብ ካልሆነ በሚልና የግል ፍላጎታችንን ለማስፈጸም ባለን ፍላጎት በግጭቱ ለማሸነፍ እንድንታገል በማድረግ በመሸነፍ የማሸነፍ ሚስጥር እንዲጠፋብን አይናችንን ሊጋርድ የሚችል መሆኑ ነው። "ተሳስቻለሁ" እና "አጥፍቻለሁ" የሚሉ ቃላትን እንዳንጠቀምና ዝቅ ብለን በመሸነፍ ግጭቱ በሰላምና በእርቅ እንዲደመደም ጥረት እንዳናደርግ ልባችን በትዕቢትና በእልከኛነት እንዲሞላ ሊያደርግ ይችላል። የማሸነፍ መንፈስ የተጠናወታቸው ጥንዶች

አጋጣሚውን እየፈለጉና እየተጠቀሙ በቃላት ጦርነት ቤታቸውን ያተራምሱታል:: ልባቸው በጉዳት ይሰበራል:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ወድቀው ለእርቅና ግንኙነታቸውን ለማደስ ጥረት ከማድረግ ይልቅ በሰላም ተቀምጠው እንዳይነጋገሩና ችግራቸውን እንዳይፈቱ ልባቸው የከበደባቸው ባለትዳሮች የግጭት አሉታዊ ተጽዕኖ ሰለባዎች ናቸው። ለትዳራችን ሰላም እንዲመጣ የትዳር አጋሮቻችንን ገንዘብ በማድረግ ግንኙነታችን ጤናማ እንዲሆን ከፈለግን *"እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን"* /**፩ኛቆሮ** 6፡ 7/ የሚለውን የሐዋሪያው ጳውሎስን ምክር ልንሰማ ይገባል::

በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ወደ አለመግባባትና ግጭት በማደግ ጥንዶችን በስሜት ተጎዳድተው እንዲራራቁ ያደርጓቸዋል:: በአካል እንዲለያዩ ብሎም ግንኙነታቸው በፍች እንዲደመደም በማድረግ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያመጡም ይገኛሉ። ትንሽ አለመግባባት እያደገ በመሄዱ ምክንያት በሚፈጠር ግጭት የክርስቲያን ባለትዳሮች መለያየትና ብሎም ወደ ፍች መድረስ በየቤተ እምነታችንና በየአጥቢያችን እየተለመደ የመጣና በየዕለቱ የምንሰማው ከፍተኛ የሆነ የትዳር፣ የቤተሰብ፣ የቤተ ክርስቲያንና የሕብረተሰብ ተግዳሮት ሆኗል። እግዚአብሔር በነብዩ በኩል እንዲህ ሲል ፍችን እንደሚጠላ ይናገራል፡- *"መፋታትን እጠላለሁ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፥..."* /**ሚል** 2፡ 16/። ነገር ግን ብዙዎቻችን ለራሳችን ፍላጎት እንጂ ለመለኮት ፈቃድ ሕይወታችንን ባለማስገዛታችን የአሳብ ልዩነት ወደ አለመግባባት፤ አለመግባባት ደግሞ ወደ ግጭት፤ ግጭት ደግሞ ወደ ፍች እያደገ እግዚአብሔር የሚጠላውን የሚወዱና የሚያደርጉ ጥንዶች በዝተው እንዲታዩ አድርጓል::

በግጭት ምክንያት በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠረው ተጽዕኖ አሉታዊ ብቻ አይደለም:: ግጭት መልካም የሆነ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳለውም ማየት ይበልጥ ተጠቅመንበትና ተምረንበት ለማለፍ እንድንችል የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ለባለትዳሮች በመካከላቸው የሚፈጠረው አለመግባባትና ግጭት ከግል ሕይወታቸው፣ አስተሳሰባቸው፣ ባህሪያቸው፣ ልምምዳቸው ጀምሮ በግንኙነታቸው ውስጥ ለውጥ የሚያሻው ጉዳይ እንዳለ አመላካችና የማንቂያ ደወል ሊሆን ይችላል። በትዳር ውስጥ ባለው ግንኙነት ከብዙ አቅጣጫ ብዙ ነገሮች እየተለወጡ፣ እርምጃ እየተወሰደባቸው ባለትዳሮች ተስማምተው ያቋረጧቸው፣ ያስወገዷቸውና ሌላ ጊዜ እንዲህ አይቀጥልም የተባባሉባቸው ነገሮች እንዳሉ ሁሉ እንዲሁም ወደ ፊት ለውጥ የሚፈልጉ ብዙ ጉዳዮች አሏቸው:: ግጭት መፈጠሩ በጥንዶቹ መካከል ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች የሚጠቁም ስለሚሆን ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን አካባቢወች ለመለወጥ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ነው። የተበላሹ የመኪና መንገዶችን ለማስተካከል ሌላ የተሻሉ አማራጭ መንገዶች መሥራት ሲጀመር ***"በሥራ ላይ"*** ፤ ***"በማንባታ ላይ"*** ና ***"በጥገና ላይ"*** የሚሉ ምልክቶች ይቀመጣሉ:: ያኔ ቀስ ብለን በዝግታ ወደ ምንሄድበት ቦታ ሊያደርሱን





የሚችሉ ሌሎች አማራጭ መንገዶች ካሉ እነርሱን በመጠቀም የአሁኑ መንገድ እንዲህ ሁኖ መቆፋፈሩን እያየን ለተሻለ ለውጥ ነው በማለት በትዕግስት እናሽከረክራለን። በማንኛውም የትዳር ዘመን ያሉ ጥንዶች በሙሉ የትዳር ሕይወታችን በግንባታ፣ በሥራና በለውጥ ሂደት ላይ እንዳለ አምነን ልንቀበል ይገባል። ይህ ከገባን የትዳራችን ግንኙነት ይበልጥ እንዲጠነክር ለለውጥ አጥብቀን እንድንሠራ ያደፋፍረናል።

ሌላው የግጭት አዎንታዊ ገጽታ በግጭቱ መፈጠር ያለፍንባቸውና የምናልፍባቸው ተሞክሮዎች የሚሰጡን ትምህርት ነው። የትዳር ሕይወት አንዱ መመረቅ የሌለበት ትምህርት ቤት ነው። በትዳራችን መካከል የሚፈጠሩት ግጭቶች አስመርረውን ሳይሆን አስተምረውን እንዲያልፉ ተማሪ የመሆን ፈቃደኝነት በማሳየት ግንኙነታችንን መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

**ግጭት አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ እንዳይፈጥርብን ከግጭቱ ሂደት ተማሪ እንጅ ተመራሪ እንሁን!!**

ብዙ ጊዜ የምንጋጨውና በግጭቱ ወቅትም ለማሸነፍ ከፍተኛ ጥረት የምናደርገው የግል ፍላጎታችንን ለማስፈጸም በሚደረግ ጥረት ነው። ራስ ተኮር የሆነው ማንነታችን ዋና የግጭት መንስኤ ነው። ነገር ግን የትዳር ግንኙነት የራሳችንን ግለ ፍላጎት የምናስጠብቅበት ሳይሆን ለሌላው ማለትም ለትዳር አጋሮቻችን ፍላጎት ለመኖር ራሳችንን የምንሰጥበት ነው:: ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በ፲ቆሮ 7 *"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።"* **ቁ** 3 *" ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ።"* **ቁ** 4 እና *"... እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ"* **ቁ** 5 በማለት የሚያስተምረን:: የክርስቲያን ትዳር መሠረት አጋፔያዊ ፍቅር ነው:: አጋፔ ፍቅር ደግሞ ራሱን አሳልፎ ለሌላው በመስጠት መሥዋዕት የሚሆንና በራስ ወዳድነት የማይጠመድ ፍቅር ነው። *"ፍቅር ...የራሱንም አይፈልግም..."* /**፩ኛቆሮ** 13፡ 4-7/:: ጋብቻ ባለትዳሮች በዚህ ፍቅር ላይ ተመሥርተው የየራሳቸውን የግል ፍላጎት በመተው ለትዳራቸው ጤናማነትና ሰላም አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለማርካት የሚጥሩበት ተቋም ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሁልጊዜ የራሳችንን ኃላፊነትና ግዴታ ያሳየናል እንጅ ሌላው አካል ለእኛ እንዲያደርግልን የምንሟገትበት ምንም ዓይነት ድጋፍ አይሰጠንም።

ሌላው የግጭት አዎንታዊ ተጽዕኖ ግጭትን በጋራ እየፈቱ በሚጓዙበት ወቅት ባልና ሚስት የሚያገኙት ከፍተኛ የሆነ ልምድ ነው። ለዚህም ነው በቅርብ ያገባን ሰዎች ከቆዩ ባለትዳሮች ለመማር መዘጋጀት ያለብን። ያሳለፍናቸው የተለያዩ የትዳራችን ተግዳሮቶች እንድንለወጥ ተገዳድረውን፣ እንደ ጎበዝ ተማሪ መልካም አሠራርንና አኗኗርን ተምረንባቸውና ነገ ለሚፈጠሩ ግጭቶች ልምድ አግኝተንባቸው ካለፍን ጥበበኞች ነን። ግጭቶች እርስ በርሳችንም ይበልጥ እንድንተዋወቅ እድል ስለሚሰጡን በብዙ ነገሮች

ከቀድሞ በበለጠ እየተረጋጋንና ስጋት እየቀነሰን እንድንመጣ ያግዙናል። አንድ ጊዜ ባለቤቴ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ባልተግባባንና በተጋጨን ወቅት ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ ተነጋግረንና ይቅርታ ተጠያይቀን ይበልጥ ከትናትናው በበለጠ መፈላለጋችን ሲጨምርና ግንኙነታችን ሲጠንክር ስትመለከት፡- "እንዲህ መጋጨት ፍቅርን የሚጭምርና ግንኙነትን የሚያጠናክር ከሆነ ለግጭት ፕሮግራም እናውጣ!" አለችኝ፡፡ ይህ ተሞክሮ የሚያሳየን ግጭትን ፈልገን እናምጣው ወይም እንውደደው የሚል ሳይሆን ባጋጠመንና በትክክል መፍታት በቻልን ጊዜ በእኛ ግንኙነት ውስጥ ያመጣውን መልካምና ገንቢ የሆነውን ተጽዕኖ ነው።

ግጭትን በአግባቡ፣ ብስለትና ጥበብ በተሞላው መንገድ መፍታት ከተቻለ በየጊዜው ለሚፈጠሩብን ግጭቶች እውነተኛ መንስኤዎችን ለይቶ በመረዳት ከምንጩ ለማድረቅና ለማሸነፍ በጋራ ተስማምቶ ለመሥራት መነሳትን ይፈጥራል። የመጣው ችግር ትዳራችንንና ግንኙነታችንን ለማፈራረስ የሚገዳደረን ነውና የማፍረስ ተጽዕኖውን እምቢ ለማለት መንቃት አለብን፡፡ እንዲህ አይነት ንቃትና አስተዋይነት ካለን ሊያፈርሰን የመጣው ተግዳሮት በጋራ አንዱ ሌላውን እያሸፈነና እየረዳ እንድንመላለስ ያስተምረናል። የትዳራችንን ጉዳይ በምንም ሁኔታ አንዳችን ከሌላችን ጋር ***"የራስህ (የራስሽ) ጉዳይ ነው!"*** በሚል እልከኝነት የምንገፋፋበትና የምንጣጣልበት አይደለም፡፡ እንዲህ አይነቱ የመጣጣል ችግር ሰይጣን ጥንዶችን በየግል ለይቶ የሚመታበትና አንድነታቸውን ለማፈራረስ የሚጠቀምበት ዘዴ ነውና ነቅተን ግንኙነታችንን መጠበቅ ኃላፊነታችን መሆኑን አንዘንጋ! በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የትዳር አጋሮቻችን ጉዳይ ሕይወታችንና ጉዳያችን ነውና!!

## II. በባለትዳሮች መካከል የግጭት አይቀሬነት

### 1. ተፈጥሯዊ ልዩነታችን

ስለ ሰው ተፈጥሯዊ ማንነት የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን በመልኩ እንደ አምሳሉ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው"* /ዘፍ 1፡ 26-27/ ይላል። ይህ አፈጣጠራችን በወንድ እና በሴት መካከል ያለውን አንድነታችንና ልዩነታቻንን ያመለክተናል። አንድነታችን ከሌሎች ፍጥረታት ተለይተን በእግዚአብሔር መልክና አምሳል መፈጠራችን፣ ሕያው ነፍስ ያለን መሆናችንና ለአዳም እንደ እርሱ ዓይነት ረዳት አልተገኘለትም በሚሉ የተለያዩ መግለጫዎች ተብራርቷል። ወንድና ሴት ሆነን መፈጠራችን ደግሞ ልዩነታችንን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ማንሳት የፈለኩት በትዳር መካከል አለመግባባትና ግጭት አይቀሬ እንዲሆን ያደረገው አንደኛው ምክንያት ተፈጥሯዊ ልዩነታችን መሆኑን ነው። ተፈጥሯዊ ልዩነት በውስጡ የተለያዩ ዝርዝር ልዩነቶችን እንደሚያካትት መረዳት አስፈላጊ ነው።

#### 1) ጾታዊ ልዩነት





እግዚአብሔር ሰዎችን ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥር በዓላማ፣ ተመሳሳይነትና ልዩነት እንዲኖራቸው አድርጎ ፈጥሯቸዋል። በትዳር ውስጥ ስንኖር የወንድና የሴትን ተፈጥሯዊ ተመሳሳይነትና ልዩነት መረዳት ካልቻልን ለማያቋርጥ ግጭት ተጋላጭ እንሆናለን። የመጀመሪያው ልዩነት ስነ ልቦናዊ ነው። የፔኒሲሊፌናያ ዩኒቨርስቲ ጥናት *"ሴቶች አእምሮቸው ከብዙ ነገር ጋር የተገናኘ እንደሆነና በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታ ማሰብ፣ መገናኘትና መሥራት እንደሚችሉ ይገልጻል"*፡፡[4] አብዛኛው የወንድ ልጅ አእምሮ አንድ ነገር ሲያስብ ወይም አንድ ነገር ላይ ብቻ ሲያተኩር ብሎም በውጥረት ወቅት ብዙ ማሰብና መናገር የማይፈልግ ሲሆን አብዛኛዎቹ ሴቶች በተቃራኒው አእምሮቸው በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታ መሄድ፣ ማሰብ፣ መሥራትና በውጥረት ወቅት በማውራት ስሜታቸውን መግለጽና መፍትሔ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ይችላሉ። ለምሳሌ ሴቶች ብዙ የኮምፒዩተር ዊንዶ ከፍተው በአንድ ጊዜ መሥራት ሲችሉ ወንድ ልጅ ግን አንድ ዊንዶ ከፍቶ ከዚያ ሲጨርስ ሌላ ዊንዶ በመከፈት መጠቀም እንደሚመርጠው ማለት ነው። ሚስቶች በቤት ውስጥ በአንድ ጊዜ ብዙ ሥራ መሥራት ሲችሉ ባሎች አንዱን ስራ ስንጨርስ ወደ ሌላው እንቀጥላለን እንጅ ብዙ የተለያዩ ሥራዎችን በአንድ ጊዜ የመስራት ተፈጥሮ የለንም።

ባለትዳሮች ወንድና ሴት ሁነው መፈጠራቸው ሊያመጣ የሚችለውን ልዩነት፣ ለውጦችና ተጽዕኖዎች መረዳት መቻል አለባቸው። ጾታዊ ልዩነት በባለትዳሮች አካላዊ አቋም፣ ስሜት፣ አስተሳሰብ፣ ማሕበራዊ ግንኙነት፣ የግብረ ስጋ ግንኙነትና አካላዊ ንጥረ ነገሮች (ሆርሞን) ይታያል፡፡ ይህም ደካማና ጠንካራ ጎናቸው ላይ ልዩነት መፍጠሩ የግድ ነው። ጾታዊ ልዩነት የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመረዳት፣ በመተሳሰብና በልበ ሰፊነት ግጭትን በትክክለኛ መንገድ ለመቆጣጠር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ልዩነቱን አስቀድሞ መረዳት የተፈጠረና ሊፈጠር የሚችል ግጭት በባለትዳሮች ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮ እንዳያልፍ ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ይጠቅማል።

#### 2) የዕድሜ ልዩነት

በባለትዳሮች መካከል ግጭት አይቀሬ እንዲሆን ከሚያደርጉት ሌሎች ምክንያቶች አንዱ በጥንዶች መካከል ሊኖር የሚችል የዕድሜ ልዩነት ነው። በባለትዳሮች መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት በጥንዶች መሰረታዊና አስፈላጊ በሆኑ ፍላጎቶቻቸው፣ ዋጋ በሚሰጧቸው እሴቶች፣ በችሎታቸውና በአስተሳሰባቸው (እይታቸው) ላይ ግልጥ የሆነ

---

[4] Jason Howerton, The Difference Between Men and Women's Brains Revealed? http://www.theblaze.com/stories/2013/12/02/the-difference-between-men-and-womens-brains-revealed Dec. 2, 2013 accessed March. 26, 2014

ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል። አንዳንድ ሰዎች በኑሮ ላይ ያለባቸውን ጫና ለማቃለልና ችግራቸውን ለማስወገድ የአባትና የልጅን፣ የእናትና የልጅን የሚያክል የዕድሜ ልዩነት እንዳላቸው እያወቁ ወደ ትዳር ይገባሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ወደ ትዳር የገቡ ጥንዶች የእድሜ ልዩነት በመካከላቸው አለመግባባትና ግጭት ሲፈጥርባቸው ይታያል። አንዳንዶች በዓላማ ለተወሰነ ጊዜ በትዳር በመቆየትና ሰበብ ፈልገው በመለያየት ንብረት ተካፍለው ኑሯቸውን በመቀየር ቃል ኪዳናዊ የሆነውን ትዳር ወደ ኮንትራት ጋብቻ ይቀይሩታል። የዕድሜ ልዩነት የሚያመጣውን ግጭትና አሉታዊ ተጽዕኖ በመረዳት ልዩነትን ማጥበብና የትዳርን ግንኙነት በማጠናከር ግጭትን መቀነስ፣ እንዲሁም በትክክለኛ መንገድና በብስለት ግጭትን መፍታት አስፈላጊ ነው።

3) **ቴምፐራመንት** (ስብዕና)

አንድ ሰው ሲወለድ የራሱ ተፈጥሯዊ ማንነት አለው። ከአንድ እናትና አባት የተወለዱ ልጆች የተለያየ ተፈጥሮ ይታይባቸዋል። *"የእናት ሆድ ዥንጉርጉር"* እንዲሉ ከአንድ ወላጅ የተወለዱ ልጆች የተለያየ ስብዕና ካላቸው ከተለያየ ቤተሰብ የመጡ ሁለት ጥንዶች የስብዕና ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል መገመት ከባድ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው ራሱን የቻለ ብርታትና ደካማ ጎን አለው። **የመጀመሪያው** የስብዕና ልዩነት አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች፣ ከአካባቢውና ከሁኔታዎች ጋር ራሱን በቀላሉ የማስለመድና አብሮ የመኖር ዝንባሌ ሲኖረው ሌላኛው ሰው ደግሞ ቁጥብና በቀላሉ ከአካባቢውም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር ለመዋሃድ የሚቸገር ሰው ይሆናል፡፡ ይህም ማሕበራዊ ግንኙነታቸው የተለያየ ለመሆኑ አንዱ ምስክር ነው። **ሁለተኛው** ልዩነት አንድ ሰው ሌላውን ሰው ለመቆጣጠር ወይም በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር ለመሆን የመፈለግ ዝንባሌ ሊኖረው የሚችል መሆኑ ነው። **የመጨረሻው** ልዩነት አንድ ሰው ፍቅርን ከሌላው የሚፈልግበትና ፍቅርን ለሌላው የሚገልጽበት ስሜት የተለያየ መሆኑ ነው፡፡[5] እነዚህን የመሳሰሉ ልዩነቶችን መገንዘብ ከሌላ ሰው ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር አስፈላጊ ነው።

እነዚህን የመሳሰሉ ልዩነቶች ምክንያት ሆነው ከተለያየ ቤተሰብና አስተዳደግ የመጡ ጥንዶች የመጋጨት እድላቸው ሰፊ እንዲሆን ያደርጉታል። ጥንዶች ከአካባቢያቸው ጋር ለመመሳሰልና ማሕበራዊ ግንኙነት ለመፍጠር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ መቻልም አስፈላጊ ነው። ምሳሌ ለመጥቀስ ያክል፡- ባል በማሕበራዊ እንቅስቃሴ ሂደት ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመጡ የሚፈልግ እንጂ እርሱ ወደ ሰዎች መሄድ የማይፈልግ ሊሆን ይችላል። ሚስት በተቃራኒው በአብዛኛው ማሕበራዊ ግንኙነት ላይ የምትገኝ ብቻ ሳትሆን በብዙ ነገር

[5] Arno, Richard G. Temperament Theory. National Christian Counselour Assosation (NCCA) Sarasota: Fl, 1994. Page3.



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

የማሕበሩን ትኩረት የምትስብ ቶሎ የምትቀላቀል ልትሆን ትችላለች። ባንድ ወቅት የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ባልና ሚስቶችን በማማከርበት ጊዜ ባል ከጠቀሰው ችግር አንዱ ሚስቴ ከእኔ ይልቅ ማሕበራዊ ነገር ታበዛለች፡፡ በማሕበራዊ ስበሰባ ላይ ብቻየን በመቀመጥ ባይተዋር እሆናለሁ፡፡ ከሚስቴ ይልቅ ሌሎች በደንብ ይንከባከቡኛል የሚል ነበር፡፡ እኔም ሚስት የሞላችውን ፎርም በመመልከትና በግል በመጠየቅ ከባህርይዋ ማሕበራዊ ነገር እንደምትወድ አረጋገጥኩ። ከዚያም የሌላውን ተፈጥሯዊ ባህርይ ለመረዳትና ነገሮችን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለማየት አንዱ በሌላው ላይ ትኩረት እንዲያደርጉና ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ በማሳየትና የቤት ስራ በመስጠት ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ መያዝ እንደሚፈልጉ ተነጋግረን ተለያየን። አንዳንድ የትዳር አጋሮች ቤት ውስጥ ብቻቸውን ሲሆኑ አቅም ሲያገኙና ሲደሰቱ ሌላው አካል ደግሞ በሰዎች መካከል ሲሆንና በሰዎች ሲከበብ ደስተኛ ይሆናል።

ከዚህም ባሻገር አንዱ ሌላውን የመቆጣጠር ዝንባሌ ሲኖረውና በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር መሆንን የማይፈልግ ሲሆን የመቆጣጠር ሙከራ ከተደረገበት ሊቆጣ፣ ሊጋጭና ዐመጽ ሊያስነሳ ይችላል። እንዲህ አይነት የስብዕና ልዩነት ባለበት ቦታ "ሚስት ለባሏ ትገዛ" የሚለው ጥቅስ ባለትዳሮችን ሲያጋጭ ይታያል። አንዳንዶች ደግሞ ማንንም የመቆጣጠር ስብዕናና ፍላጎት የላቸውም፤ ከዚህ የተነሳ ብዙ ነገር ሲበላሽ ዝም ማለትን ይመርጣሉ፡፡ በትዳራቸው የሚኖራቸው ኃላፊነትና ሚናም የተገላቢጦሽ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች ማንንም መቆጣጠር አይፈልጉም ነገር ግን ራሳቸው በአንድ ስልጣን ቁጥጥር ስር ሆነው መታዘዝና መገዛት ይፈልጋሉ። ሌላውን የመቆጣጠር ፍላጎት ያላቸውና በሌሎች ቁጥጥር ስር መሆን የመፈለግ ተፈጥራዊ ስብዕና ያላቸው ሰዎች መኖራቸውን መረዳት ካልቻልን በትዳር ላይ ግጭት መፈጠሩ የማይቀር ነው፡፡ ግጭቱም ኃይለኛና ቶሎ የማይበርድ በመሆን ግንኙነቱን ወደ ማይፈለግ አቅጣጫ ሊቀይረው ይችላል።

ጥንዶቹ አንዱ ከሌላው ፍቅር በሚፈልጉበት ጊዜ ፍላጎታቸውን ለመግለጽ ሁኔታዎች ካልተመቿቸውና እርስ በርሳቸው ካልተረዳዱ የሚፈልጉትን በማጣት የማይፈልጉት ሲፈጠርባቸው ሊበሳጩ ደግሞም እንዳልተወደዱና ተቀባይነት እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ። በተቃራኒ ጾታ ፍቅር ከትዳር አጋሮቻቸው የሚፈልጉትና የሚሰጡት አለመመጣጠን ከተፈጠረና ፍቅራቸውን የሚገልጹበት ቋንቋ የተለያየ ሆኖ አለመግባባት ካለ ግጭት እንዲፈጠር ሁኔታዎች ምቹ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ችግር ያጋጠማቸው ባለትዳሮች የትዳር አጋሮቻቸውን ከሌሎች የትዳር አጋሮች ጋር በማወዳደር ይበልጥ ሊጎዱና ሊጋጩ ይችላሉ፤ ይህም ለመለያየት ጠንቅ ሊሆን ይችላል። ወደ ትዳር ዓለም የገባናው ከትዳር አጋሮቻችን ጋር አንድ ዓይነት ሰው እንድንሆን ሳይሆን ልዩነታችንን፣ ጠንካራና ደካማ ጎናችንን በመረዳት ተዋደን፣

ተቀባብለን፣ ተሳስበንና በጋራ ግጭቶቻችንን እየፈታን አንዳችን ሌላችንን በመጥቀም ለመኖር ነው።

## 2. የተለያዩ የግል ፍላጎቶች

በጥንዶች መካከል ግጭት እንዳይጠፋ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ ጥንዶች የየግል የሆነ የተለያየ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች መሆናቸው ነው። የፍላጎት ልዩነት እንዳይግባቡ፣ እንዲጋጩና እንዲለያዩ ሊያደረግ ይችላል። የፍላጎት ልዩነት ብቻ ሳይሆን በጥንዶች መካከል ተመሳሳይ የሆነ ፍላጎት መኖሩም ሌላው የግጭት መንስኤ ሊሆን የሚችል ጉዳይ ነው። ከተመሳሳይነቱ የተነሳ ለእኔ ይሁንና የእኔ ይቅደም በሚሉ ጥያቄዎች፣ የጥንዶችን ተመሳሳይ የሆነ የየግል ፍላጎት ለማሟላት የገንዘብ፣ የጊዜና የጉልበት አቅም ሊኖር ስለማይችል ግጭት ይፈጠራል ግጭቱም ሊባባስ ይችላል።

በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች አብረው ያሳለፉት ጊዜ አጭር ከመሆኑ የተነሳ፣ የሰው ልጅ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ ስለሚለዋወጥና እርስ በእርስ ሙሉ በሙሉ ተዋውቀው ስለማይጨርሱ አንዱ የሌላውን ትክክለኛ የሆነ የግል ፍላጎት ለማወቅ መቸገራቸው ጭምር ችግሩ አይቀሬ እንዲሆን ያደርገዋል። አንዱ የሌላውን ፍላጎት አለማወቅ ብቻ ሳይሆን ፍላጎትን ለማሟላት የሚደረገው ጥረትም በቂ ካልሆነ አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለማሟላት፣ ለማርካትና ለማስደሰት የሚያደርገው ጥረት ተመጣጣኝ አለመሆን ወደ ግጭት ያመራል፡፡ እንዲሁም በነገሮች ያለመርካት ችግር መታየት በየጊዜው በመካከላቸው ግጭት እንዲነሳ፣ ግጭቱ እንዲሰፋና እንዳይጠፋ ሊያደርገው ይችላል።

*"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።"* /**1ኛ ቆሮ** 7፡ 3/

## 3. የእሴቶች ልዩነት

እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ዋጋ የሚሰጠው ጉዳይ አለው። እሴቶች ለልዩ ልዩ ጉዳዮች የምንሰጣቸው ዋጋዎች ናቸው፡፡ እያንዳንዳችን ለሰው፣ ለቤተሰብ፣ ለግንኙነት፣ ለጊዜ፣ ለገንዘብና ለንብረት፣ ለሥራ፣ ለትምህርት፣ ለመንፈሳዊ ሕይወትና ለአገልግሎት፣ ለወዳጅነትና ለራሳችን የምንሰጠው ዋጋ የተለያየ መሆኑ በዚህ ልዩነት ምክንያት አለመግባባትና ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ እንዲሆን ያደርገዋል። እሴቶቻችን በአስተዳደጋችን፣ በምንማረው፣ በልምምዳችን፣ በእምነታችንና ምናልባትም በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ሊወሰኑ፣ ሊቀረጹ፣ ሊያድጉና ሊሻሻሉ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ "ግድ አይሰጥህም/ሽም/"፣ "ይኼኔ እንዲህ እናድርግ ቢባል ኖሮ"፣ "ምንድን ነው የሚያስደንቅህ/ሽ/"፣ "ለምንድን ነው ለዚህስ ጉዳይ ስፍራ የማትሰጠው /ጭው/?" ... የሚሉ ንግግሮች በግንኙነታችን መካከል እየተንጸባረቁ አለመግባባቶችን ወደ ከፋ ግጭት እንዲደርሱ ሲያደርጉ የሚታዩት በእሴቶቻችን ላይ ባሉን ልዩነቶች ምክንያት ነው፡፡





## 4. ወደ ትዳር ሕይወት የገቡበት የተሳሳተ ምክንያት

ሌላው በባለትዳሮች መካከል አለመግባባትና ግጭት እንዳይጠፋ ብሎም መለያየት እንዲፈጠር ከሚያደረጉ ምክንያቶች አንዱ ሰዎች ስለትዳር ያላቸው የተሳሳተ መረዳት ነው። ፍቅርን ለትዳር መሠረት አድርጎ ወደትዳር ከመግባት ይልቅ በሌሎች በተለያዩ ነገሮች ላይ መመሥረት ወይም ወደ ትዳር ዓለም የሚገቡባቸው የተለያዩ የተሳሳቱ ምክንያቶች መኖራቸው ማለትም የግብረ- ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን ለማርካት ብቻ፣ ልጅ ለመውለድ ካላቸው ብርቱ ፍላጎት በመነሳት፣ የኢኮኖሚ ችግሮቻቸውን ለማስወገድ፣ በውጭ አገር የሚኖሩ የኢሚግሬሽን ጉዳይ ለማስፈጸምና አገር ቤት ያሉ ወደ ውጭ አገር ለመውጣት፣ በተለይ በእህቶች ላይ የሚታይ የዕድሜን ፍርሃት ለማምለጥ፣ የቤተሰብንና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ግፊትና ጫናን ለመግታትና ምላሽ ለመስጠት በማሰብ ወደ ትዳር መግባት በትዳር ውስጥ ግጭት እንዳይጠፋ ሊያደርግ የሚችል ምክንያት ነው።

ወደ ትዳር ዓለም ለመግባት የሚያስቡ ወገኖች ስለጋብቻ ትክክለኛ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት በማግኘት ወደ ትዳር ለመግባት በእውነተኛ ፍቅር መዋደድን በማረጋገጥ እንዲሁም ትክክለኛ የሆነ በጋራ ለመረዳዳት የሚያስችል ኅብረት መኖሩን በመገንዘብ እንጂ በአንዱ አካል ብቻ ለመረዳት በሚያስብ ፍላጎትና ምክንያት ወደ ትዳር ላለመግባት ቆም ብሎ ማሰብና መጠየቅ፣ መጸለይና ማማከር አስፈላጊ ነው። ወደ ትዳር ዓለም ያልገቡ ወጣቶች ለምን ማግባት እንደፈለጉ ትክክለኛ ምክንያት እንዲኖራቸው ብቻ ሳይሆን ሊያገቡት የሚያስቡትን ግለሰብ ለትዳር የመረጡት ለምን እንደሆነ መነሻ ሃሳባቸውንና ምክንያታቸውን በመፈተሽ ትክክለኛ ምላሽ ሊያገኙ ይገባል። ይህንን ማድረጋቸው ወደ ትዳር በሚገቡበት ወቅት የግጭትን መንስኤዎችን መቀነስ እንዲቻልና በትዳር ውስጥ ደስተኛ የትዳር ሕይወትና ጤነኛ ግንኙነት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽ ይሰጣል።

## 5. ከትዳር ተጠብቆ የሚገባው ተስፋ (ግምት)

በግንኙነት ላይ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በሚገባ ተቆጣጥረን ገንቢ በሆነ መንገድ ተምረንበትና ተለውጠንበት የማለፍ ስኬታማነታችንን ጥበቃችን ይወስነዋል። አንዳንዶች ከትዳርና ከትዳር አጋራቸው ጠብቀው የሚገቡት ነገር ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ እንደጠበቁት ሳይሆን ሲቀር ይጎዳሉ፡፡ ስለትዳር አጋሮቻቸው "የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውን? " ፤ "አብረን መሄድ የማንችል ሰዎች ነበርን እንዴ? " እና "ምንድን ነው የተሳሳትኩት?"... በማለት መጠየቅ ይጀምራሉ። አንዳንዶቹ በትዳር ውስጥ ሁልጊዜ ደስታ፣ ጤነኛነት፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት... እንደሚኖር እየሰሙና እያሰቡ ማደጋቸው፤ ጥበቃቸው ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎት ሊሆን ይችላል። ሳይሟላ ሲቀርም ክፉኛ ይጎዳሉ፡፡

ሕጻናት ልጆችን እወዳለሁ፣ በተቻለ መጠን ላቀርባቸውና ላጫውታቸው እሞክራለሁ እነርሱም ደስ ይላቸዋል፡፡ ነገር ግን እንዲህ የማጫውታቸው ሕጻናት የሽንት ጨርቃቸው /ዳይፐራቸው/ በወላጆቻቸው የተቀየረላቸው፣ የታጠቡና የተመገቡ ናቸው። ሰዎች ልጆችን ስታጫውት ጎበዝ ነህ ሲሉኝ እንዲህ እላቸው ነበር ዳይፐሩ የተቀየረለትና ንጹህ የሆነ ሕጻን ማጫወት እወዳለሁ እላቸዋለሁ። የሚያምር አያያዝ የተያዘን ሕጻን ልጅ ሌላ ሰው አዘጋጅቶ ሰጥቷቹህ ማጫወትና ራሳችሁ አጥባቹህ፣ ልብሳቸውን ቀይራችሁና መግባችሁ ማጫወት ፈጽሞ የተለያዩ ልምምዶች ናቸው። ትዳር እንዲህ ዓይነት ሥራና ድካም እንዳለው ካላሰብንና ካልጠበቅን በስተቀር ልጆችን እንደ ስጦታ ሳይሆን እንደ መከራ ልናያቸው እንችላለን። አንዳንዶች ትዳር የእያንዳንዳችንን ሥራ የሚጠይቅ ግንኙነት እንደሆነ አስበው ወደ ትዳር አለመግባት መሠረታዊ ችግራቸው ነው፡፡ ትዳር ተብሎ ሲታሰብ ሁልጊዜ እየተሠራን የምንሠራበት ተቋም እንደሆነ ጠብቀን ወደ ትዳር አለመግባት በሚፈጠረው ግጭት እጅግ በጣም ተጎጅዎች እንድንሆን ያደርገናል።

አንዳንዶችን ለእንዲህ ዓይነቱ ከፍተኛ የሆነ ተስፈኝነት ተጋላጭ ሊያደርግ የሚችለው መልካሙን የትዳር የሕይወት ገጽታ ብቻ በሚመሰክሩ ባለትዳሮችና በሚያስተምሩ የጋብቻ አስተማሪዎች የሚፈጠረው ሚዛናዊ ያልሆነ ተጽዕኖ ነው፡፡ በጓዳቸው ውስጥ ቀውስ በቀውስ ሆነው በሰው ፊት ግን ትዳርን ምንም ችግር የሌለበት ዓለም የሚያስመስሉ ጥንዶችና ኑሯቸውና የሚሠሩት ፊልም ፈጽሞ የተለያየ የሆነባቸው የፊልም ተዋናያንኖች መካከል ከፍተኛ መመሳሰል አለ፡፡ ሁለቱም ከእውነታው ዓለም ጋር የሚመሳሰል ነገር ግን ከገሃዱ ዓለም ፈጽሞ የራቀ ተውኔት ያሳዩናል፡፡ በዚህም ሥራቸው በምናየው ፊልም ተጽዕኖ ስለትዳር የተዛባ ግምት እንዲኖረንና ግምታችን እንዲበላሽብን ያደርጋሉ፡፡ የጠበቅነው ተስፋ እውነት አለመሆኑን ስናውቅም ከፍተኛ ጉዳት ውስጥ እንወድቃለን።

ሌላው ችግር ከትዳር ዝቅተኛ የሆነ ጥበቃና ተስፋ ይዞ ወደ ጋብቻ መግባት ነው። ስለትዳር ከቤተሰቦቻቸው እያዩ ካደጉት በመነሳት፤ በሌሎች የታወቁ በሚባሉ መንፈሳዊ ሰዎች ትዳር ከሚፈጠረው ግጭት፣ መለያየትና ፍች፤ አንዳንድ የጋብቻ አስተማሪዎችና አማካሪዎች ይበልጥ የጥንዶችን ኃላፊነት ለማሳየት በሚያደርጉት የማስጠንቀቂያና የማስፈራሪያ ትምህርትና ምክር ምክንያት ትዳርን ፈጽመው አጨልመው የሚያዩ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ እንዲሁም በዓለም ላይ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ የሚታየው ከፉ የሆነ አፍራሽ ተጽዕኖ አንዳንዶች ስለትዳር ያላቸው ግምትና ተስፋ እንዲደበዝዝ ብሎም እንዲጠፋ ያደርጋል።

ስለትዳር ያለን የተሳሳተ ጨለምተኝነት በዚህ ዘመን በጋብቻ ጸንቶ መቆየት አይቻልም የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንድንደርስ ያደርገናል! የሰማናቸው አሉታዊ አስተሳሰቦች ትዳርን እንደ እስር ቤት እንድንቆጥርና ትዳር መልካም ነገር የሌለበት





የውጥረት ዓለም ነው የሚል ከንቱ አስተሳሰብ እንዲኖረን ተጽዕኖ ያሳድሩብናል፡፡ በላጤነት የነበሩ ብዙ ጊዜያዊ ነጻነቶችንም እንድንናፍቅ ይቀሰቅሱናል፡፡ እነዚህን በመሳሰሉ ከንቱ ምክንያቶች በትዳር ውስጥ ያለው በረከት ተካፋይ ሳንሆን እንዳንቀር በጋራ ተዋድደን፣ ተቀባብለንና ተረዳድተን በመኖር በትዳራችን በታማኝነት ለመዝለቅ ሚዛናዊ የሆነ ግንዛቤ፣ ጥበቃና ግምት ሊኖረን ይገባል። በከፍተኛ ጥበቃ በአየር ላይ እንዳንንሳፈፍ ደግሞም በዝቅተኛ ግምት ፈጽሞ ነገር ሁሉ ተገላቢጦሽ ሆኖብን በትዳር ቀውስ እንዳንሰቃይ ሚዛናችንን ጠብቀን መሬት መርገጥ ይሻለናል።

## 6. የችሎታና ልምድ አለመኖር

እያንዳንዱ ሰው የተለያየ ችሎታና ልምምድ አለው። ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ችሎታና ልምምድ ሊኖረው አይችልም። የትዳር ግንኙነት አስፈላጊ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ ባለን የተለያየ ችሎታና ልምምድ እርስ በርስ ለመረዳዳት እንድንች ነው። በትዳር ግንኙነት ውስጥ ጥንዶች እርስ በርሳቸው አንዱ የሌላውን ችሎታና ልምድ መለየትና መረዳት ካልቻሉ አንዱ ሌላውን እንዲመስል፣ እንደሌላው እንዲሰራና እንዲለማመድ የሚያደርጉት ጥረት ግጭት እንዲፈጠርና አብሯቸው እንዲሰነብት ሊያደርግ ይችላል።

ጥንዶቹ በጋብቻ የቆዩበት ዘመን አጭር ከመሆኑ የተነሳ አንዱ የሌላውን ችሎታና የግል ልምምድ ለመረዳት ሊቸገሩ ይችላሉ። ምናልባት ይህ ደረጃ አንዱ የሌላውን ማንነት፣ ችሎታና ልምምድ ለማወቅና ለመረዳት ጥረት የሚያደርጉበት ወቅት ሊሆን ይችላል። በጋብቻ ውስጥ የትዳር አጋር ችሎታዎችና ልምዶች በተለያዩ ደረጃዎችና ራሳቸውን በቻሉ ወቅቶች የመታየት ባህርይ እንዳላቸው መረዳት ያስፈልጋል። በቅርብ በተጋቡ ጥንዶች ሕብረት ውስጥ ግጭት እንዳይጠፋ ከሚያደርገው ምክንያት አንዱ ያሉበት ደረጃ አንዳቸው የሌላቸውን ችሎታ፣ ክህሎትና ልምድ ለማወቅ ጥረት የሚያደርጉበት ወቅት መሆኑን መገንዘብ አለመቻላቸው ነው።

ችሎታዎችና የተለያዩ ልምዶች ልንማራቸው የምንችላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ ለማወቅ፣ ለመማርና ለመለወጥ ዝግጁ መሆን ተገቢ ነው። ሁሉን ለማወቅ መማርና መልመድ አለብህ/ሽ/ በሚል ግትርነት እንዳንጋጭ አንዱ የሌላውን ጉድለት በመሙላትና በመረዳዳት በልዩነት ያለውን ውበት አድምቀን ለማሳየት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። እዚህ ላይ አንድ የራሴን ልምድ ላካፍላችሁ፡- እኔ ለብዙ አመታት በቤተሰብ ቤትና በምግብ ቤት እየፈረምና እየገዛ ይመገብ የነበረ እንዲሁም በትምህርት ቤት ውስጥ ፎርም ይዞ በመማር እዚያው እየተመገበ ያሳለፍኩ ከዚያም በጋብቻ ውስጥ ለተወሰነ ዓመት ምግብ ማብሰል የማይችልና ምግብ የማብሰል ፍላጎትም ያልነበረው ሰው ነበርኩኝ፡፡ አንድ ቀን በየወሩ በመገናኘት የምንማርበትና የምንመካከርበት የባለትዳሮች ፕሮግራም ላይ በተነሳ አንድ ጥያቄና በአንዲት እህት ማበረታቻ ቀላል ነገር ማለትም

ቁርስ ከዚያም ሌሎችን ነገሮች በተለይ ሚስቴ የምትወደውን ጥቂት ነገር ማብሰልና ማቅረብ ጀመርኩ።

በዚህ ምግብ የማብሰል መልመድ ሂደት ከፍተኛ እገዛ ያደረገልኝ አንደኛው ምክንያት የመጀመሪያዋ እህት ማበረታቻ ነው፡፡ ነገር ግን በተለይ የምሰራው ሁሉ ለሚስቴ የሚጥማትና የምትወደው መሆኑ ትልቅ የሞራልና የጽናት ስንቅ ሆኖኛል። በዚህ ወቅት ምግብ ማብሰል መልመድ መቻሌ ባለቤቴ ባረገዘችና በወለደች ወቅት እንዳንቸገር ጠቅሞናል። የማልችለውን ለመልመድ እኔ እንዲህ መለወጥ ከቻልኩ እንደ እኔ ልምድ የሌላችሁ ልትለምዱና ልትማሩ የምትችሉት ብዙ ነገር አለ ማለት ነው! ችሎታውና በቂ ልምድ ያለው የትዳር አጋር ሌላውን ሰው ለማስተማርና ለማሰልጠን በልበ ሰፊነት እድል ሊሰጥና ደግሞም አንድ ሰው ተሳስቶና አበላሽቶ የሚማርና የሚሻሻል ፍጡር መሆኑን ሊያስተውል ይገባል።

## 7. ግልጥ ኃላፊነትና ሚና አለመኖሩና ካለም ደግሞ እንደሚገባ አለመወጣት

ጋብቻ የተለያየ የሥራ ኃላፊነትና ሚና ያለበት ተቋም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ አድርጎ እንደሚያስቀምጠው በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት የየራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ እርሱ ባል (ወንድ)እርሷ ደግሞ ሚስት (ሴት)ናቸው፡፡ ለልጆቻቸው የአባትነትና የእናትነት ኃላፊነት አለባቸው /ኤፌ 5፡ 21-31 እና 6፡ 1-4/። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ኃላፊነትና ሚናን አለመረዳትና መወጣት አለመቻል በዚህ የተነሳ የሚፈጠሩ ችግሮች (ግጭቶች) እንዳይበርዱ ያደርጋል። ግልጥ ባልሆነው ሚናቸው ምክንያትም ባልና ሚስት ያለአግባብ ጥቅስ እየተማዘዙ የሌላውን አካል ሚና ለማሳወቅ፣ ለማሳመንና ለማዘዝ በሚያደርጉት ጥረት ጠብ ውስጥ ይገባሉ። የተፈጠረው ጠብና ንትርክም ልጆች ሲወለዱ ልጆችን ተንከባክቦ በማሳደግ የአባትነትና የእናትነት ሚናን በመወጣት ሂደት ውስጥ የባሰ ግጭት እንዲፈጠር ሊያደረግ ይችላል።

ጥንዶች በጋብቻ ሕብረት ውስጥ ገና መኖር የጀመሩ ከመሆናቸው የተነሳ በቤት ውስጥ ያላቸው የሥራ ኃላፊነት ብዙም ግልጥ ላይሆን ይችላል። ምናልባትም ከባህል አንጻር የሴቶችና የወንዶች የሥራ ድርሻ በማለት ሥራን ሊከፋፈሉ ይችሉ ይሆናል። በእርግጥ የወንድና የሴት የሥራ ድርሻ የሚለውን ልምዳችንን እንድንለውጥ ተጽዕኖ የሚያደርጉብን የአመለካከትና የሁኔታ ግፊቶች በየጊዜው መፈጠራቸው አይቀሬ ነው፡፡ በተለይ ከአገር ውጭ የምንኖር ወገኖችን የዘመን መለዋወጥ፣ የምንኖርበትን አገር ውጥረትና ኑሮን የማሸነፍ ትግልና የምንሠራቸው ልዩ ልዩ ሥራዎች ጫናዎች በጾታ ሳይሆን በችሎታ፣ በልምድና ጊዜ ያለው ሰው ሥራዎችን እንዲሠራና በጋራ የሥራ ኃላፊነታችንን እንድንወጣ እያስገደዱን ናቸው፡፡ ቢሆንም ግን ሁሉም ሰው ወደ ለውጥ መጥቷል ማለት አይደለም። ከልጅነቴ ጀምሮ ሥራ አይወድም እየተባልኩ ያደግሁና ሌላ ሰው በሚሠራው ሥራ በማትረካ ባለሙያ እናት እጅ ያደገ ሰው ከመሆኔ የተነሳ ከቤት





ውስጥ ሥራዎች እጅግ በጣም የራቅሁ ሰው ነበርኩ፡፡ ነገር ግን በትዳር ዓለም እንዲሁ መቀጠል የሚቻል ሆኖ አላገኘሁትም።

የግድ ባለቤቴን ማገዝ፣ ልጆቼን ማሳደግና የጋራ ቤታችን ውስጥ በጋራ መንቀሳቀስ አለብን! ነገር ግን አሁንም የተለያዩ ቢሎችን እንድከፍል ኃላፊነት በተደጋጋሚ ሲሰጠኝ ኃላፊነቱን እሺ ብዩ ብቀበልም እንኳ እስካሁን ምክንያቱን በገልጥ ባላውቅም ቢሎችን የመክፈሉን ሥራ ተሳክቶልኝ ተወጥቸው አላውቅም። በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ ጊዜ ባለቤቴ እኔ ምን አገባኝ መብራቱንና ስልኩን፣ ኢንተርኔቱን፣ የቴሌቪዥኑን መስመር ይቁረጡት በማለት ትዝተብኛለች፡፡ በኋላ ግን ልሠራው ያልቻልኩትን ሥራ እርሷ አቀላጥፋ ትፈጽመዋለች። እስካሁን በቤታችን ጉዳይ ከውጭ ሥራዎች ጋር የምታገናኘን እርሷ ናት፡፡ ነገር ግን **"የቤታችን የውጭ ጉዳይ ክብርት ሚኒስቴር"** እንድትሆን የቀረበላትን የእኔን የባሏን ሹመት መቀበል አልፈለገችም፡፡ ምክንያቱም ሹመቱን የሰጠሁበትን መነሻ አሳብ አሳምራ ታውቀዋለች!!

ለምሳሌ ለመጥቀስ ያክል እንደ አጋጣሚ ሆኖ በቤት ውስጥ ቤትን መጥረግ፣ ማጽዳትና ልብስ ላውንደሪ ማድረግ በመጠኑም ቢሆን ደስ የሚለኝና በአብዛኛው እኔ የምሠራው ሥራ ሲሆን እርሷ ደግሞ እነዚህን ሁለት ነገሮች በመጠኑም ቢሆን ትጠላለች። የባለቤቴን የሥራ ዩኒፎርም ይበልጥ እንዲነጻ በሚል በጎ ሃሳብ ለነጭ ልብስ ማንጫ በማይሆን ባለቀለም የሆኑ ልብሶች ላውንደሪ ላይ በመጠቀም ብዙ ዩኒፎርሞቿን ዝንጉርጉር በማድረግ ያበላሸሁባት ቀናትም ትዝ ይሉኛል። ለእርሷ ደግሞ ምግባችንን በማብሰል፣ ፍላጎታችንን በማወቅና ወደ ገበያ ወጥታ አስፈላጊ የሆኑ የቤት ወጭዎችን በማድረግ አስቤዛ፣ ፍጆታና ዕቃዎችን መግዛዛትና ማቅረብ ተጠቃሽ ኃላፊነቶቿ ናቸው።

## 8. በየጊዜው የተለያዩ ለውጦች በባለትዳሮች መካከል መፈጠር

ጥንዶች ተፈጥሯዊ የሆኑ አካላዊ ለውጦች አሏቸው። በዚህ ሂደት ውስጥ ለውጦች ለግጭት ምክንያት ግጭቶችም ለለውጥ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። በጥንዶች ሕይወት በተፈጥሯዊ  የሰውነት ንጥረ ነገር (ሆርሞን) በተለይ ደግሞ በሴቶች ላይ በየወሩ የሚከሰት በወር አበባ ምክንያት የስሜት፣ የጸባይና ሌሎች ከወር አበባ ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ሁኔታዎችን ጥንዶቹ በጋራ መረዳት ካልቻሉ ወቅታዊና ቀጣይነት ያለው ግጭት መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ሌላው ከሆርሞን ጋር በተያያዘና በዕድሜ መጨመር ምክንያት፣ በክብደት መጨመርና መቀነስ፣ በእርግዝና፣ በልጆች መወለድ፣ ከስራ በመቀነስ የመሳሰሉ ምክንያቶች ለውጦች ድንገት ሳይታሰቡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ታቅደው ሊፈጠሩ ይችላሉ። ጥንዶች የተለያዩ ለውጦችን ለማስተናገድ እንዲችሉ ቅድመ እውቀቱ፣ ዝግጅቱ እንዲሁም ለውጡን ለማስተናገድ ፈቃደኛነቱ ከሌላቸው ግጭት መፈጠር ብቻ ሳይሆን ግጭቱ ተባብሶ ወደማይፈለግ ሌላ አቅጣጫ ሊለወጥ ይችላል።

ሌላው አስቸጋሪ የሆነውና ለሌሎች ችግሮች አሳልፎ ሊሰጥ የሚችለው ለውጥ የባሕርይ ለውጥ ችግር ነው። ባለትዳሮች በየጊዜው የሚቆጡ፣ የማይግባቡ፣ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ቁጣቸውን መቆጣጠር የማይችሉ፣ ትንሹን ነገር ትልቅ በማድረግ የሚናደዱና ሲናደዱ የሚያደረጉትን የማያውቁ ሰዎች መሆን ሲጀምሩ በቤተሰብ ውስጥ ያልታሰቡ ቀውሶች ይፈጠራሉ። ሌላው ከፉ ቀውስ የሚፈጠረው ራስ ወዳድነት የሚባለው የተደበቀና የተገለጠ ባሕርይ  ሲኖር ነው። ከትዳር አጋር ይልቅ ለራስ፣ ከእኔ፣ ለእኔ፣ በእኔ በኩል ብቻ የሚሉ ግለኝነትን ማዕከል ያደረጉ ባሕርያት ትዳርን ከፉኛ የሚያቃውሱ ጠንቆች ናቸው። በራስ ወዳድነት የተጠመደ ማንነት ያለው የትዳር አጋር ቀናተኛ፣ ነገሮችን ሁሉ ልቆጣጠር የሚል፣ እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ባይና አምባገነንነት የሚያጠቃው ነው። ይህ ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ባለትዳሮች *"በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤"* /ፊል 1፡ 2/ የሚለውን የጳውሎስ ምክር በመዘንጋት በእኔነት ታውረው መስማማት ሲያቅታቸውና ሲጋጩ ይታያሉ።

በከፉ እኔነት የተጠመዱ ባለትዳር የሆኑ ሰዎች ለሌላው አካል የሚያደርጉትን ሁሉ በከንቱ ውዳሴ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ነገር ግን ከትዳር አጋራቸው ይልቅ እንደሚሻሉ የሚያስቡና የሚቆጥሩ፣ ከትዳር አጋራቸው ይልቅ ለግል ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ትኩረት የሚሰጡና የክርስቶስን ምሳሌነት ከመከተል ይልቅ የሚያስነቅፉ ሁነው ይታያሉ /ፊል 2፡ 1-5/። በትዳራችን መካከል የተፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች እንዲሁም ለመስማማት በሚደረገው ሂደት ይቅርታ ማድረግን ለመለማመድ እንድንቸገር ያደረጉንን ምክንያቶች በፐርሰንት እናስቀምጥ ብንል ሊያመዝን የሚችለው የእኔነታችን ጉዳይ መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም።

## 9. የመንፈሳዊ ብስለት ልዩነት

በጥንዶች መካከል አንድነትና ልዩነት ከሚንጸባረቅበት ጉዳይ አንዱ መንፈሳዊ ማንነታችን ነው። መንፈሳዊ ብስለታችን እንደ ክርስትና ዕድሜያችን ወይም በክርስትና ሕይወት በቆየንበት ዘመን መጠን ለመማር፣ ለማደግና ለመለወጥ እንዳለፍንባቸው ሂደቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ በዙሪያችን ያሉ ሰዎችና ሌሎችም ሁኔታዎች ሁሉ ተጨማምረው ብስለታችን ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ማምጣታቸው አይቀሬ ነው። በእነዚህ ምክንያቶች ባልና ሚስት በተመሳሳይ የመንፈሳዊ ብስለት ደረጃ ላይ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህም ልዩነት እይታቸው፣ እሴቶቻቸውና ራዕዮቻቸው ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል። ልዩነቶችን በመቻቻልና አንዱ ከሌላው ለመማር በተዘጋጀ ማንነት ማራመድ ካልቻሉ ግጭት መኖሩ የማይቀር ነው፡፡

በቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን ለነበረው አለመግባባትና መከፋፋል ምክንያቱ በወቅቱ የነበራቸው መንፈሳዊ ሕጻንነት ወይም አለማደግ ነበር። *"እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን?*





*እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?"* /1ኛቆሮ 3፡ 1-3/፡፡ መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር ጠብ የበዛበት ትዳር ጠብን ልምምድ ያደረገ ቤተሰብን እንደሚያፈራና በብዙ ጥላቻና መከፋፈል የተሞላች ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር አስተዋጽዖ ሊያደረግ እንደሚችል መገንዘብ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ የመልካም ቤተ ክርስቲያን መሠረት የሚጣለው መልካም ትዳር ባላቸው ጥንዶችና ባፈሯቸው መልካም የቤተሰብ አባላት ላይ ነው።

## 10. ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ ከትዳርና ከቤተሰብ ይልቅ በሌሎች ጉዳዮች መጠመድ

በሕይወት፣ በኑሮና በማሕበራዊ ጉዳይ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ኖረው ነገር ግን ቅድሚያ መሰጠት ያለበትን ነገር እንደሚገባ ባለመረዳትና ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ አንዱ የትዳር አጋር ጽንፈኛ ሲሆን፣ በጥብቅ ቁጥጥር ሥር ሲሆን ወይም በትዳሩና በቤተሰቡ የሚተካው እንቅስቃሴ ወይም ልምምድ ሲኖር ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው። ቃሉም እንደሚናገረውና እንደሚያዘው *"ሊሠራ የማይወድ አይብላ..."* /2ኛተሰ 3፡10/፡፡ ነገር ግን በዚህ ከፍል ለግጭት ምክንያት ሊሆን የሚችለው አንዱ የትዳር አጋር ከመጠን ባለፈ በሥራ ላይ ጊዜውን ሲሰጥ፣ ትኩረት ሲያደርግ፣ በሥራ የመጠመድ ሱሰኛ ሲሆን፣ ለእርሱ ሥራ ማለት ሁለንተናውና የራሱ ዓለም ሲሆንበት ነው።

አንዳንዶች ደግሞ እግዚአብሔር ለጥንዶቹ የጋራ ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሰጦታ አድርጎ ልጆችን ሰጥቷቸው ሳለ አንዱ የትዳር አጋር የግል ልጆች እስኪመስሉ ድረስ በልጆች ላይ ልዩ ትኩረት ሲያደርግና ለልጆች ብቻ ጊዜውን፣ ትኩረቱንና ሁለንተናውን ሲሰጥና የትዳር አጋሩን ችላ ማለት ሲጀምር  ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ነው። ማገልገል እንደ ክርስቲያን አስፈላጊና እግዚአብሔርም ሆነ ቤተ ክርስቲያን የሚጠብቁብን ኃላፊነት ነው። ነገር ግን አንዳንዶች ደግሞ ከመጠን በማለፍና ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ በአገልግሎትና በቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ፕሮግራሞች መጠመዳቸውና ትዳርንና ቤተሰብን ችላ ማለታቸው ግጭት ሊፈጠር ይችላል። በአጠቃላይ ከትዳር አጋርና ከቤተሰብ ይልቅ ሚዛናዊ ባልሆነና ጽንፈኝነት በተሞላው መንገድ በሌሎች እንቅስቃሴዎች፣ ነገሮች፣ ልምምዶች፣ ግንኙነቶችና ፕሮግራሞች ላይ መጠመድ ወይም መወሰድ ጥንዶችን ለግጭት ሊያጋልጣቸው ይችላል።

**መልካም ምስክርነት ላላት ቤተ ክርስቲያን መሠረት የሚጣለው መልካም ትዳር ባላቸው ጥንዶችና ባፈሯቸው መልካም የቤተሰብ አባላት መሆኑን አንዘንጋ!!**

## 11. የሰይጣን ውጊያ

በትዳር ሕይወት ውስጥ የምንኖረው የሰይጣንን አሳብ በመሳትና የእርሱን ተጽዕኖ ዝቅተኛ አድርገን በማየት መሆን እንደሌለበት እንድትገነዘቡ እወዳለሁ። ከፍጥረት መጀመሪያ ባለትዳሮችን በኃጢአት ያሳሳተ፣ እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን እንዲወቅሱና እንዲያመካኙ በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን መልካም ግንኙነት ያበላሸ የአሳቹ ሰይጣን ተጽዕኖ ነው። አሁን ባለንበት ዘመን ዓለም በከፉ እንድትሞላ፣ በብዙ ከፉ ተጽዕኖ ምክንያት የብዙዎች ትዳር እንዲፈርስ፣ ቤተሰብ እንዲበተንና ቤተ ክርስቲያን እንድትዳከም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።

አሁንም በባለትዳሮች መካከል ጠብን በመዝራት፣ አንዱ ሌላውን እንዳይረዳ በማድረግ፣ በብዙ የኃጢአት ፈተና እንዲወድቁ ወጥመድ በማዘጋጀት፣ የይቅርታ ልብ እንዳይኖራቸው በእኔነት በመሙላት፣ መለያየትና መፋታት በማንኛውም ሁኔታ የሚፈቀድና ቀላል እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ ቅዱሳንን እየተፈታተነ ይገኛል። ብዙ ሁኔታዎችን በመጠቀም ባለትዳሮች ለትዳር አጋሮቻቸው ታማኝ እንዳይሆኑ፣ የከበረው የሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች አንድነት የሆነውን ትዳር በከፍተኛ ሁኔታ በተመሳሳይ ጾታ ትዳር እንዲለወጥ ዘመናዊነትንና ሰብአዊነትን እየተጠቀመ ያለበት ዘመን ነው። በአጠቃላይ የተዋረደውን እንደ ከቡር፣ አመጹን እንደ ጽድቅ፣ የሚያሳዝነውን እንደሚያስደስት እያደረገ ትዳርን፣ ቤተሰብንና ቤተ ክርስቲያንን እየተገዳደረ ይታያል /1ኛጴጥ 5፡ 8-9/





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሁለት (2)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስንና የግል የትዳር ግንኙነት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የግጭትን ምንነት በመተርጎምና በማብራራት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ተወያዩ፡፡
2. ከአጠቃላይ የግጭት ተጽዕኖ ምንነትና በግል የትዳር ሕይወታችሁ የተፈጠሩትን የተለያዩ ተጽዕኖዎች በመጥቀስ የግጭትን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ለእውነተኛ ለውጥ ለመጠቀም በግልጥነት ውይይት አድርጉ፡፡
3. በባለትዳሮች መካከል አለመግባባትንና ግጭትን አይቀሬ ያደረጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? በእናንተ የትዳር ግንኙነት ውስጥ ግጭት እንዳይቀር ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው? እንዴትስ ልዩነቶችን በመረዳት ግጭትን በአግባቡ መፍታት ይቻላል ትላላችሁ?
4. በእናንተ የትዳር ሕይወት በአብዛኛው ጎልቶ ለግጭት ምክንያት የሚሆነውን ጉዳይ ለይታችሁ በማውጣትና የመፍትሔ እርምጃው ምን መሆን እንዳለበት በመፈለግ ግልጥና ሰፊ ውይይት አድርጉ፡፡
5. በዚህ ዘመን ሰይጣን ትዳርን፣ ቤተሰብንና ቤተ ክርስቲያንን እየተዋጋ ያለበትን የተለያየ ዘዴ በመጥቀስ እንደ ክርስቲያን ባለትዳርና ቤተሰብ ከግል ትዳራችሁ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ምን ሊደረግ ይገባል ትላላችሁ?

# ምዕራፍ ሶስት(3)

# ግጭትን በወቅቱ በጋራ ያለመፍታት የሚፈጥረው ተጽዕኖ

በማንኛውም የጋብቻ የዕድሜ ክልል ያሉ ባለትዳሮች መካከል አለመግባባትና ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ መሆኑ የምንስማማበት ጉዳይ ነው። ግጭቶች አሉታዊና አዎንታዊ ገጽታዎችን ይፈጥራሉ። አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በአግባብ ካልፈታናቸውና ካልተቆጣጠርናቸው ደግሞ በጥንዶች ላይ ፈጥረዋቸው ሊያልፉ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም። ይህ ምዕራፍ ግጭቶች በማስተዋልና በብስለት በጋራ መፍትሔ ካለተፈለገላቸው በጥንዶች የተለያዩ የሕይወት አቅጣጫዎች ላይ ሊፈጥሯቸው የሚችሏቸውን ተጽዕኖዎች የመረዳትና የመጠንቀቅ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ባለትዳሮች የግጭቶችን ተጽዕኖዎች ቀንሰው ጤነኛ ትዳርና በመልካም ግንኙነት ላይ የተገነባ ቤተሰብ እንዲኖራቸው የሚያስችል ግንዛቤን ማስጨበጥ የዚህ ምዕራፍ አብይ ዓላማ ነው።

## 1. በጥንዶች የፍቅር ግንኙነት ላይ

በየጊዜው በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች ከሚፈጥሩት አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ መካከል አንዱ በጥንዶች መካከል በነበረ፣ ባለና ሊኖር በሚገባው የፍቅር ግንኙነት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ማምጣት ነው። ግጭት በአግባቡ ካልተፈታ የጋብቻ መሠረት የሆነውን እውነተኛ ፍቅር እያደገ፣ እየበሰለና እየጨመረ እንዳይሄድ፣ ባለበት እንዲቀጥልና ፈጽሞ እንዲጠፋ ሊያደረግ ይችላል። ጥንዶች በጋራ ተሳስበው እንዲኖሩ አንቀሳቃሽና ዘላቂነት ያለው መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያደርገውን ፍቅር ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አፍራሽ ተጽዕኖ ያሳርፍበታል። ባለትዳሮች አውቀዋቸው ትዳራቸውን ከእነዚህ ችግሮች ለመጠበቅ ይችሉ ዘንድ የግጭት በጊዜ አለመፈታት በባለትዳሮች ሕይወትና የትዳር ግንኙነት ላይ ከሚያሳድራቸው አፍራሽ ተጽዕኖዎች ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንቃኛለን፡-

### 1. ፍቅርን የማቀዝቀዝ

ፍቅር በጋብቻ ውስጥ እንደ ከትባት አንዴ ወስደነው ከዚያ እንዲሁ የምንኖረው አይደለም፡፡ ፍቅር በጋብቻ ውስጥ በየጊዜው አንዱ ለሌላው በመጠንቀቅ፣ በራስ ወዳድነት ሳይሆን ለሌላው በማሰብና በመኖር፣ በተለያዩ ጉዳቶች ላይ በመነጋገርና በይቅርታ፣ አብሮ ጊዜ በማሳለፍና አንዱ የሌላውን ፍላጎት በመረዳትና በማሟላት የምንጠብቀው፣ የምናሳድገውና የምንንከባከበው ኑሮ ነው። በየጊዜው ተመሳሳይና የማያቋርጥ አለመግባባትና ግጭት የሚበዛበት ትዳር በጥንዶቹ ሕይወት ፍቅርን የማቀዝቀዝ ተጽዕኖ አለው። *"ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።"* /ማቴ 24፡ 12/ ግጭት በባለትዳሮች መካከል ፍቅርን የማቀዝቀዝ አቅም እንዳለው በመረዳት ፈጥኖ ከዚህ ችግር ለመውጣትና ፍቅርን ለማደስ የጋራ ጥረት ማደረግ ተገቢ ነው። *"ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና። እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው አወስዳለሁ።"* /ራዕይ 2፡ 4-5/ በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ሃሳብ ለጌታ ያላቸውን ፍቅር ቢገልጡም ነገር ግን በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት በጥንዶች መካከል የቅርብ ግንኙነት መጥፋት ከጀመረና ፍቅር ከቀዘቀዘ ለጌታ እውነተኛ ፍቅር የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም እወድሃለሁ ያሉትን ጌታ የማስደስት ሕይወት በመምራት ላይ እንደማይገኙ የሚጠቁም ነው፡፡ በእርግጥ የተጠቀሰው ክፍል በቀጥታ በትዳር ውስጥ ስላለ ፍቅር የሚናገር ሳይሆን በአማኞች መካከል ስላለ ፍቅር የሚናገር ነው። ነገር ግን ማስተዋል ያለብን የመጀመሪያዎቹ በቅርባችን ያሉ አማኞች የትዳር አጋሮቻችን መሆናቸውን ነው። ይህንን ክፍልም የጠቀስኩት አንድ ሰው ለትዳር ጓደኛው ፍቅር የሌለው ከሆነ ለሌሎች ወገኖች ብሎም ለክርስቶስ ኢየሱስ ያለው ፍቅር ቀዝቃዛ መሆኑንና የበለጠ የመቀዝቀዝ እድል እንደሚኖረውም ለማስጨበጥ ነው። በቅርቡ ያለውን የትዳር አጋሩን የማይወድድ ሰው በርቀት ያሉ ወገኖች እና ክርስቶስን እወድዳለሁ ሊል እንዴት ይችላል!

### 2. አለመተማመንን የመፍጠር

ግጭት በአግባቡ ካልተፈታ ጥንዶቹ በፍቅርና እርስ በርስ በመተማመን ይኖሩበት የነበረው የትዳር መርሆ እንዲቀየር የማድረግ ተጽዕኖ አለው። እውነተኛ ፍቅር በጥንዶቹ መካከል ሲኖር አንዱ ሌላውን በማመን የመቀባበል ሕይወት ጎልቶ ይታይባቸዋል። እውነተኛ ፍቅር ሲኖር ባለመተማመን የሚፈጠርን ፍርሃት አውጥቶ ይጥላል። በማማከር አገልግሎት ከገጠሙኝና ካደመጥኳቸው ንግግሮች መካከል *"ከእንግዲህ ማመን ይከብደኛል" "እንዳላምነው/ናት/ ሊደረገኝ"፣ "አምኖ አብሮ መኖር ከበደኝ"* እና *"አመኔታ የምትጥልበት አይደለም"* የሚሉ የተለያዩ ቃላቶች ይገኙበታል፡፡ *"ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።"* /1ኛዮሐ 4፡ 18/ *"ፍቅር ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደረጋል"* ይላልና /1ኛቆሮ 13፡ 7/ አለመግባባትና ግጭት በባለትዳሮች መካከል የነበራቸውን የእውነተኛ ፍቅር ባሕርይ መገለጫ የሆነውን መተማመንን ወደ ፍርሃትና አለመተማመን ይለውጣል።

### 3. ግንኙነትን የማሻከር

ሌላው የግጭት አሉታዊ ተጽዕኖ በባለትዳሮች መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ማሻከርና መልካም ተግባቦት እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው። ግጭት በፍቅር ተሸፍኖና ተቻችሎ የመኖር መርህ ተለውጦ በጠብና በጥላቻ ለከፍተኛ ጠብ ለመፈላለግ ተጋላጭ ሊያደረጋቸው ይችላል። በባለትዳሮች መካከል በቀላል ግንኙነት፣ በነፃነት፣ በበጎ ህሊና፣ በቀጥተኛነትና የውስጥን ስሜት በግልጥነት በማቅረብ ተገንብቶ የነበረው ተግባቦታቸው ወደሻከረ ግንኙነት በመሻገር ፍቅርን በማጥፋት ጠብን የሚያባብስ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። ግጭት የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቸልታ የሚታይ ሳይሆን በማስተዋልና በብስለት ልንቆጣጠረውና ልንፈታው የሚገባ ነው።

## 4. ከትዳር አጋር ይልቅ የግጭቱ መንስኤ ላይ እንዲያተኩሩ የማድረግ

በባለትዳሮች መካከል የሚጋጩበት ርዕሰ ጉዳይ ዋና ምንጩ ከራስ ወዳድነት ጋር የተያያዘ በሆነ ወቅት ግጭቱን በጋራ ከመፍታትና ለትዳር አጋር ቅድሚያ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ ችግሩ ላይና የግጭቱ መንስኤ ላይ በማተኮር ይበልጥ ግጭቱ እየጨመረ እንዲመጣ ያደርጉታል:: እርስ በእርስም ሊጎዳዱ ይችላሉ። በተለይ ተድላን ከመውደድ የሚመነጭ ግጭት ቶሎ ላያባራና ጥንዶቹ ከትዳር አጋራቸው ይልቅ ራሳቸውን፣ ገንዘብን፣ ንብረታቸውን እንዲሁም ድሎትን የበለጠ በመውደድ ላይ ብቻ ሊያተኩሩ ይችላሉ:: ለትዳር አጋራቸው ግድ የማይሰጣቸው፣ መለያየትን የሚመርጡና ቤተሰባቸውን መበተን ምንም የማይመስላቸው እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል። *"ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ "* /**2ኛጢሞ 3፡ 2-4**/

## 5. መተሳሰብና መፈላለግ እንዲቀንስ የማድረግ

ትዳር ጥንዶች በጋራ እየተሳሰቡና በፍቅር እየተፈላለጉ የሚኖሩት ኪዳን ነው። የአለመግባባትና የግጭት ምክንያት የሆኑ ችግሮች በጊዜው እልባት ካላገኙና በይቅርታ መስማማት ካልተቻለ በስተቀር ባለትዳሮች ያላቸውን የእርስ በርስ መተሳሰብና መፈላለግ እንዲቀንሱ ብሎም መተሳሰብ ከመካከላቸው እንዲጠፋ የሚያደርግ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ። እንደ ባለትዳር አንዱ ለሌላው ማሰብ ቀንሰው ግለኝነትን የሕይወት መርህ ያደርጋሉ:: ግለኝነትን የሕይወት መርህ ማድረግ ደግሞ በተገኘው አጋጣሚ እንደ ባልና ሚስት የመፈላለግ ጥረት እንዲጠፋ የማድረግ አቅም አለው። *"ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።"* /**1ኛቆሮ 13፡ 4-7**/

## 6. አብሮ የመቀመጥና የማውራት ልምድ እንዲጠፋ የማድረግ

የጋራ የሆነ ጊዜ መመደብና አጋጣሚዎችን እየፈለጉ መገናኘት እንዲሁም ተቀምጦ በመልካም ግንኙነት ማውራት የጤናማና የደስተኛ ባለትዳሮች መለያ ነው። አለመግባባትና ግጭት ሲበዛና በየጊዜው በአግባብ ሳይፈታ ሲቀር በጋራ ትዳራቸውን ለመገንባት ሲነጋገሩ የነበሩት ጥንዶች መራራቅ ይመርጣሉ:: አብረው ከተቀመጡ የሚያወሩት የሌላቸው ይሆናሉ:: ማውራት ከጀመሩ ደግሞ ለከፋ ግጭት ተጋላጭ ይሆናሉ። ችግሩ የተከሰተው አብረው እንዲቀመጡና እንዲያወሩ ሊያደርጋቸው የሚችለው ፍቅር መቀነስ ወይም መጥፋት ስለጀመረ ነው። በተደጋጋሚ በማማከር አገልግሎቴ ከሰማሁዋቸው ንግግሮች መካከል *"አብረን መቀመጥ የምንችል ሰዎች*





*አይደለንም"* ፤ *"ተቀምጠን ካወራን አያሌ ቀናት፣ ሳምንታትና ወራት አስቆጥረናል"፣ "በስንት ጊዜያችን ያውም በእኔ ተነሳሽነትና ግፊት መነጋገር ጀምረን ወዲያውኑ ስንጣላ አቆምን"፣ "ከእኔ ይልቅ በስልክ የሚያወራው /የምታወራው/ ይበልጣል"* የሚሉት ገጠመኞች የችግሩ ማሳያ በመሆን በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## II. በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ

የሰው ሁለንተና መንፈስ፣ ነፍስና ስጋ ያለው መሆኑን ከእግዚአብሔር ቃል ማየት እንችላለን /**1ኛተሰ 5፡ 23፣ ዕብ4፡ 12**/። እዚህ ላይ የምፈልገው ስለሰው ሁለንተና ለመጻፍ ሳይሆን አለመግባባትና ግጭት በባለትዳሮች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ በተመለከተ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው። የሰው ማንነት አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል። ከዚህም የተነሳ ግጭት በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ ሊፈጥር የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በዝርዝር መመልከት እንችላለን።

### 1. መንፈሳዊ

ግጭት በባለትዳሮች መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። በጥንዶቹ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚፈጠረው ተጽዕኖ ብለን ስናስብ:- **በመጀመሪያ** ባልና ሚስት በግልና በሕብረት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውና ሊኖራቸው የሚገባ ሕብረት ላይ የሚፈጠረው አሉታዊ ተጽዕኖ ማለታችን ነው። በአለመግባባት ምክንያት ቅሬታ ሲፈጠር፣ እርስ በርስ ይቅር መባባል ሲያቅታቸውና በውስጣቸው የበደለኝነት ስሜት ሲፈጠርባቸው ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ እግዚአብሔርን በቃሉና በጸሎት ከመፈለግ ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር ከሚደረግ ሕብረት መራቅ ግጭት የሚያስከትለው የባለትዳሮች የመንፈሳዊ ሕይወት ችግር ነው። በዚህ ምክንያት ቀድሞ የነበራቸው መንፈሳዊ ግለትና መነቃቃት ሊጠፋባቸው ይችላል። *"እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ። አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤"* /**ማቴ 5፡ 23-25**/

**በሁለተኛ** ደረጃ  በጊዜ ያልተፈታ ግጭት በጥንዶቹ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከቅዱሳን ጋር የሚኖራቸው ኅብረት እንዲቀንስና እንዲጠፋ ሊያደርግ መቻሉ ነው። የግል መንፈሳዊ ሕይወታቸው መድከም ሲጀምር ከቅዱሳን ጋር  ኅብረት በማድረግ በቅዱሳን የተዘጋጀውን በረከትና ጸጋ የመካፈል ትጋታቸውና ፍላጎታቸው ይቀንሳል ወይም ይጠፋል:: በሌሎች አገልግሎት ከመጠቀምና ሌሎችን ከመጥቀም ወደ ኋላ እንዲሉና ይህ ዓይነቱ መተናነጽ ግድ የማይሰጣቸው እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል።

**ሶስተኛውና** የመጨረሻው የግጭት አለመፈታት በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ የነበራቸውንና ሊኖራቸው የሚችለውን የአገልግሎት መልካም ተጽዕኖ ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረጉ ነው። በጠብና በግጭት የተሞላ ማንነትና

የትዳር ሕይወት ያላቸው ጥንዶች በግል ሕይወታቸውና በየጊዜው በቅዱሳን ሕብረት ለመልካም ሥራ የነበራቸው መነቃቃት የጠፋባቸውና ምሳሌነት የሌለው ማንነት ባለቤት ሆነው አገልግሎት ለመስጠት የሚታገሉ ይሆናሉ፡፡ ሚስጥሩ በደንብ ባይገባውም እንኳን ተገልጋዩም ለመገልገልና አገልግሎታቸውን ለመቀበል ሊቸገር ይችላል። *"ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፣ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?"* **1ኛጢሞ 3፡4-5**

## 2. አካላዊ

በጊዜው እልባት ያላገኘ አለመግባባትና ግጭት በባለትዳሮች የሰውነት (የአካል) የጤና መታወክ ሊያስከትል ይችላል። ግጭት የጥንዶችን የውስጥ ስሜት በመጉዳት ለውጫዊ አካላዊ መጎዳት ተጋላጭ ያደርጋቸዋል። በውስጣቸው ሰላምና ደስታ የራቃቸው ጥንዶች ለሌሎች በሽታዎች ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ከአሁን በፊት የተለያዩ በሽታዎች ያሉባቸው ከሆኑ በሽታዎቻቸውን ሊያባብሱ ይችላሉ። ካለመግባባትና ከመጋጨት የተነሳ ሊከሰቱ ወይም ሊባባሱ ከሚችሉ በሽታዎች መካከል:- የጨጓራ፣ የደም ግፊት፣ የስኳር ሕመም፣ ፊት ላይ የሚወጣ ማድያትና የፊት መጨማደድ የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው። በአንዳንድ ባለትዳሮች መካከል ከቃላት ባለፈ ቁጣን መቆጣጠር አቅቷቸው የሚደባደቡና የሚጎዳዱም አይጠፉም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ በዲፕሎማ የክርስቲያን ሳይኮሎጅ ኮርስ በምንወስደበት ወቅት ከተማሪዎች መካከል አንዱ በወቅቱ ለሚያስተምሩን ዶክተር ጥያቄ አቀረበ። ለጥያቄው መልስ የሚሆን ማብራሪያ በማግኘት ፋንታ "አንድ የጋብቻ አስተማሪ እንዲህ ብሎ አስተማረን" በማለት ከአስተማሪው የተማረውን ትምህርት የግል እምነቱ አድረጎ ያቀረበውን አሳብ ፈጽሞ አልረሳውም! ያ ወንድም *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /ኤፌ 5፡ 31/ የሚለውን ጥቅስ ከጠቀሰ በኋላ ከጥቅሱ "አንድ ስጋ" የሚለውን ሀረግ በመውሰድና *"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበኩሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።"* /1ኛቆሮ 9፡ 27/ ከሚለው ቃል ጋር በማቀናጀት መተርጎም ጀመረ። ያቀረበው የትርጉሙ አሳብ "ባል ሚስቱን ሊቀጣትና ሊመታት ወይም ሊደበድባት ይችላል" የሚል ሲሆን ከሌሎች ተግባራዊ ምስክርነቶች ጋር እያይዞ በማቅረብ ለማሳመን ጥረት አደረገ። በወቅቱ ከዚህ ወንድም ጋር እርሱ ያጣቀሰውን የጋብቻ ትምህርት የተማሩ ጥንዶች ወይም የሰሙ አገልጋዮች እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊያቀርበው የሞከረውን ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ መረዳትና ልምምድ የተጋሩ ከሆነ ወደ ተለያዩ አማኞች አባዝተውት ሊሆን እንደሚችል ወይም ሊያባዙት እንደሚችሉ መገመት አያስቸግርም። እንደዚህ አይነት ትምህርት፣ ልምምድና ተግባር ቁጣን መቆጣጠር አቅቧቸው አካላዊ ጉዳት ለሚያደርሱ ግለሰቦችና ባለትዳሮች አበረታችና አጽናኝ የሆነ ነገር ግን አፍራሽ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ልምምድ ነው።





## 3. ስነ ልቦናዊ

በወቅቱ በጋራ ውይይትና በይቅርታ ያልተፈታ አለመግባባትና ግጭት በባለትዳሮች ስነ ልቦና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነው። በግጭት ምክንያት በባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠሩ ስነ ልቦናዊ ጉዳቶች መካከል የተሰበረ ልብና የተራራረቀ ስሜት እንዲኖር ማድረጉ ተጠቃሽ ነው። ጥንዶችን በቁጣ፣ በንዴትና በምሬት እንዲሞሉና ለአጭር ጊዜም ቢሆን አዕምሮቸውን መቆጣጠር እንዲያስቸግራቸው ሊያደርግ ይችላል። ይህ ችግር ያጋጠማቸው ባለትዳሮች ብዙ ጊዜ በፍርሃት በመሞላት ለተስፋ መቁረጥና ላለመተማመን ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ብሎም በብዙ ነገር ድፍረት የሌላቸው እንዲሆኑ የማድረግ አቅምም አለው።

## 4. ማሕበራዊ ሕይወት

መልካም ትዳር ለመልካም ቤተሰብ፣ መልካም ቤተሰብ ለመልካም ቤተ ክርስቲያንና ለመልካም ሕብረተሰብ መሠረት ነው። የሰው ማሕበራዊ ሕይወት የሚጀምረው ከቤተሰቡ ነው። መልካም ግንኙነት የሌላቸውና ግጭት የበዛባቸው ባለትዳሮች ፈጥነው በይቅርታ መስማማትና ችግሮቻቸውን መፍታት ካልቻሉ ችግሩ ከእነርሱ አልፎ ቤተሰብን፣ ቤተ ዘመድን፣ ወዳጆችን፣ ጎረቤትንና ቤተ ክርስቲያንን የተጽዕኖው ሰለባ ማድረጉ አይቀሬ ነው።

በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠረው አለመግባባትና ግጭት ጥንዶችን ከማሕበራዊ ሕይወትና ግንኙነት እንዲርቁ፣ ራሳቸውን እንዲያገልሉ፣ ከሌሎች ማለትም ከቤተሰብ፣ ከቤተ ዘመድ፣ ከወዳጆቻቸውና ከቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲበላሽና እንዲቋረጥ ያደርጋል። በተለያዩ ሚዲያዎች እየተጠቀሙ ይከውኑት የነበሩትን ማሕበራዊ ግንኙነት ማለትም የነበራቸውን የስልክ፣ የኢሜል፣ የፌስ ቡክና ሌሎችን ማሕበራዊ ድረ ገጾችን መጠቀምን እንዲተውት ያስገድዳቸዋል። ሰዎችን የመዝጋት፣ ስልክ ቁጥርና አድራሻ ማጥፋትና ቀድሞ ሲያዘወትሩባቸው ከነበሩ ቦታዎች ሁሉ የመጥፋት ባሕርይ ሊታይባቸው ይችላል ።

በጊዜው ፈጥኖ በመወያየትና በይቅርታ እልባት ያላገኘ የባለትዳሮች ግጭት አሉታዊ ተጽዕኖው ከፍተኛ ነው። ያልተፈታ ግጭት ትንሽ የነበረው ትልቅ፣ ጥቂት የነበረው ብዙ፣ ቶሎ ሊፈታ ለሚችለው አላስፈላጊ የሆነ ጊዜ በመስጠቱ ችግሩ ያልተፈለገ አቅጣጫ እንዲይዝ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይም አሉታዊ፣ ውስብስብና አስቸጋሪ የሆነ ገጽታ እንዲፈጠር የማስገደድ አስተዋፅጾው ከፍተኛ ነው፡፡ አለመግባባትና ግጭት በማንኛውም ትዳር ውስጥ የማይጠፋ ልምምድ ቢሆንም ግጭቱን ፈጥኖ በመፍታት ሁኔታውን ወደ ሰላማዊ ግንኙነት ለመለወጥ ፈቃደኛ መሆን የእያንዳንዱ ባለትዳር የግል ኃላፊነት ነው፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን ባለትዳሮች ለዚህ ሊተጉ ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግና ኃላፊነትን ለመወጣት ከአቅም

በላይ የሆነ ችግር ካጋጠመ የሌሎችን ሰዎች አስፈላጊ የሆነ እርዳታ በማግኘት ችግሩን መፍታት በጣም አስፈላጊ ነው።

**መልካም ትዳር ለመልካም ቤተሰብ፣ መልካም ቤተሰብ ለመልካም ቤተ ክርስቲያንና ለመልካም ሕብረተሰብ መሠረት ነው!!**





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሶስት (3)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ግጭትን በጊዜው መፍታትን እንዴት ትገልጡታላችሁ?
2. ግጭት በጊዜው በአግባብ ካልተፈታ ሊፈጥራቸው የሚችላቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በመዘርዘር በሰፋት ተወያዩባቸው::
3. በትዳር ግንኙነታችሁ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በጊዜው በጋራ እንዳትፈቱ የሚያደርጓችሁን ምክንያቶችና በግልና በትዳር ሕይወታችሁ ያመጡባችሁን አሉታዊ ተጽዕኖዎች በመዘርዘር በፍጹም ግልጥነት ተነጋገሩ::
4. በጊዜው ያልተፈታ ግጭት በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመዘርዘርና የተለያዩ ምሳሌዎችና ምስክርነቶችን በመጨመር ውይይት አድርጉ::
5. በጊዜው መፈታት ያለባቸውን የግል የትዳር ግጭቶቻችሁን ቆም ብላችሁ በማሰብ ራሳችሁን መርምሩ:- ፈጥናችሁ እርምጃ ልትወስዱባቸው የሚገቡ የግጭት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ጊዜ በመበጀትና ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ፈጣን የሆነ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ በግልና በጋራ አቅዱ::

# ምዕራፍ አራት (4)
# የተለያዩ የለውጥና የሽግግር ደረጃዎች

## I. የተለያዩ የለውጥ ደረጃዎች ምንነት

ብዙ የግንኙነት ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት በባለትዳሮችም ሆነ ረጅም ጊዜ የቆየ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተለያዩ ወቅቶችን መሠረት አድርገው የሚከሰቱ ለውጦች አሉ። እነዚህ የተለያዩ ወቅቶች የሚፈጥሯቸውን የለውጥ ሂደቶች ተከትለው ከሚፈጠሩ ግጭቶች ትዳርን የመጠበቁ ስኬት እንደ ባለትዳሮች ማንነት፣ የትዳራቸው ግንኙነት እንደተመሠረተበት መሠረት፣ ወደ ትዳር ሲገቡ ከትዳር ለማግኘት እንደሚጠብቁት ጉዳይ፣ እርስ በእርስ ይበልጥ እንደመተዋወቃቸው፣ ለተለያዩ የግንኙነት ደረጃዎች እንዳላቸው መረዳትና እንደ ጥንዶች ብስለት ሊወሰን ይችላል። በተለያየ ጊዜ የሚፈጠሩ የተለያዩ ወቅታዊ የሆኑ የሽግግር ደረጃዎች መኖራቸውን መረዳትና እንደ አመጣጣቸው ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን፣ የለውጥ ሂደቶቹን ለመቆጣጠርና የሚያስከትሉትን አሉታዊ የሆኑ ተጽዕኖዎች አስቀድሞ ቢቻል ለማስቀረት ቢያንስ ደግሞ ጎጅ ተጽዕኗቸውን ለመቀነስና ተመርሮ ሳይሆን ተምሮ ለማለፍ መዘጋጀት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በትዳር የተጣመሩ ጥንዶች ሊረዷቸው የሚገቡ በባለ ትዳሮች መካከል የሚፈጠሩ የለውጥና የሽግግር ደረጃዎች ምንድን ናቸው? የሚከተሉት ነጥቦች ይህንን የሚያስዳስሱን ይሆናሉ:-

## II. በጥንዶች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ለውጦች

### 1. ሆርሞናል ለውጥ

ሆርሞናል ለውጥ በወንድና በሴት አካል ውስጥ የሚገኝ ተፈጥሯዊ የሆነ ሆርሞን በመባል በሚጠራ የተፈጥሮ ንጥረ ቅመም አማካኝነት የሚመጣ ለውጥ ነው:: በወንድ ልጅ አካል ውስጥ ቴስቶስተሮን የተባለው ንጥረ ነገር ከፍና ዝቅ ማለት የሚያመጣውና ሊፈጥረው የሚችለው አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖና የለውጥ ሂደት በትዳር ሕይወት ውስጥ ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል:: ኢስትሮጅን እየተባለ የሚጠራው በሴቶች አካል ውስጥ የሚገኝ ተፈጥሯዊ የሆነ ንጥረ ቅመም ደግሞ በሴቶች ላይ በወር አበባ ጊዜ፣ በእርግዝና፣ በወሊድና በዕድሜ ምክንያት መጨመሩና መቀነሱ የሚያመጣው ለውጥና ተጽዕኖም በትዳር ውስጥ ለሚፈጠር ግጭት አንዱ ሊጠቀስ የሚችል ምክንያት ነው:: ይህን ርዕሰ ጉዳይ ማንሳት አስፈላጊ የሆነው ጥንዶች አንዱ ሌላውን እንዲረዱና እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ ለመጠቆም ነው። የሆርሞን ለውጥ የሚያመጣውን ተፅዕኖ በመረዳት አንዱ ለሌላው አስፈላጊ የሆነ እንክብካቤ በመስጠት ግጭትን ለመቀነስና መልካም እና ሁለተናዊ የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር እንደሚቻል ጥንዶቹ ሊገነዘቡ ይገባል። በወንዶችም ሆነ በሴቶች ውስጥ ያለው ሆርሞን (በሰውነት





ውስጥ ያለ ንጥረ ቅመም) በጥንዶቹ ግንኙነት፣ ወሲባዊ መነሳሳትና መጣጣም፣ ስነ ልቦናዊ የባህሪ መለዋወጥ፣ የፍላጎትና የስሜት ለውጥ ብሎም ማሕበራዊ ኑሯቸው ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ በመገንዘብ ለትዳር ግንኙነት ጥንቃቄ ማድረግ  አስተዋይነት ነው::

### 2. አካላዊ ለውጥ

አንድ ሰው በመወለድ ይጀምርና በየጊዜው ሁለንተናዊ እድገት እያሳየ በመቀጠል በመጨረሻም በሞት ምድራዊ ኑሮው ይገደባል። የሰው ልጅ በራሱ ላይ የሚያስተናግደው አካላዊ እድገት፣ የሰውነት መጠን፣ የክብደት መጠንና የውበት ለውጥ በየጊዜው በዕድሜ መጨመርና በሌሎች የተለያዩ ጉዳዮች ምክንያት ለውጡ ሊፈጥንና ሊዘገይ ይችላል። ዕድሜ ሲጨምር፣ በእርግዝና፣ በወሊድና ልጅ በማሳደግ ሂደት ብሎም በአኗኗር ዘይቤና በምንኖርበት አካባቢ ተጽዕኖዎች የተነሳ በጥንዶቹ በተለይ ደግሞ በሴቶች አካል ላይ ለውጥ መኖሩ አይቀሬ ነው። ቀድሞ ከጋብቻ በፊት የነበረ ውበት፣ የሰውነት አቋም፣ ቅርጽ፣ ክብደት... በሚለወጥበት ወቅት ተፈቃቅሮና ተቀባብሎ በመኖር የትዳርን ግንኙነት መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ለውጥ አንጻር ነው ያላገቡ ወጣቶች ትዳርን በውጫዊ ውበት ላይ ብቻ መመሠረት የሌለባቸው። ከውጭ የጀመሩት አድናቆት ግርዶሽ ሳይሆንባቸው ውጭውን አልፈው የውስጥን ውበት በመመልከትና በማድነቅ የትዳር ውሳኔ ላይ ሊደርሱ እንደሚገባ መመከር የሚገባቸውም ለዚህ ነው!!

### 3. ስነ ልቦናዊ ለውጥ

ሰው በየጊዜው በሚያድግበትና በተለያየ ሁኔታ ውስጥ በሚያልፍበት ሂደት ከሚያጋጥሙት ለውጦች መካከል አይቀሬ ከሆኑት አንዱ በስነ ልቦና ላይ የሚፈጠር ለውጥ ነው። ከአካባቢ ጋር የስሜት ሕዋሳትን ተጠቅሞ ግንኙነት በማድረግ፣ በማንበብ፣ በመማር፣ አካበቢ በመቀየር ለተለያዩ ነገሮች ተጋላጭ በመሆን፣ በሕይወት የሚገጥሙ የኑሮ ምርጫዎች፣ ውሳኔዎችና ተግዳሮቶች ጥለዋቸው የሚያልፉ ልምምዶች፣ ስሜቶች፣ አስተሳሰቦችና እሴቶች ስነ ልቦናዊ ለውጥ እንዲኖር ያስገድዳሉ። አንዳንድ ለውጦች ማለትም የሆርሞን (የንጥረ ቅመም)፣ አካላዊና ስሜታዊ ... ለውጦች በስነ ልቦና ላይም ተጽዕኖ ማድረጋቸው አይቀሬ ነው። ለውጦችን ከተለያዩ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ጋር እንደሚገባ ለመረዳት ጥረት ማድረግ በጥንዶች መካከል በየጊዜው የሚፈጠርን ግጭት የመቀነስ አስተዋጽዖ ብቻ ሳይሆን አንዱ ሌላውን በመረዳት እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ ለማስቻል የሚሰጠው ጠቀሜታ  የጎላ ነው።

### 4. ስሜታዊ ለውጥ

የሰው ልጅ እውቀት፣ ፈቃድና ስሜት ያለው ፍጡር ነው። በሰው ሕይወት ውስጥ መደሰት እንዳለ ሁሉ የሐዘን ጊዜና ስሜት የሚቀየርባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። ጥንዶች ለመጋባት የቃል ኪዳን ውል ስንዋዋል በማግኘት በማጣት፣ በሕመም፣

በጤንነት፣ በደስታና በሐዘን በማለት በተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች ሁሉ የማይሰበር ቃል ኪዳን ገብተናል፡፡ ለዚህም ነው በምንም ዓይነት የስሜት መለዋወጥ ውስጥ ስናልፍ አንዳችን ለሌላችን ታማኝ ባልና ሚስት እንድንሆን የምንጠየቀውና ቃል ኪዳናችንን በመጠበቅ አፍቃሪ ባልና ሚስት እንድንሆን ፍላጎትና ጥረት ልናሳይ የሚገባን።

በጥንዶች መካከል በየጊዜው የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ ግጭቶች፣ የተለያዩ ያልታሰቡና ያልታቀዱ የሕይወትና የኑሮ ቀውሶች፣ የሕመም ስሜቶች፣ እርግዝና፣ በወሊድ ወቅትና ከወሊድ በኋላ የሚፈጠሩ የስሜት መለዋወጦች፣ ድብርቶችና ልጅ የአለመውለድ ችግሮች በትዳር ውስጥ ያጋጥማሉ፡፡ በተጨማሪም ነገሮች እንደታሰቡት ሳይሄዱ በመቅረታቸው ስሜታችን ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎች፣ የስሜት ለውጦች ማለትም ደስታ፣ ለቅሶ፣ መቆዘም፣ ቁጡና ንጼታማ መሆን የመሳሰሉ የሕይወት ገጽታዎች አይቀሬ መሆናቸውን መረዳት ተገቢ ነው። የስሜት ለውጥ በሥራ፣ በግንኙነት፣ በቤተሰብ፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት፣ በንግግር፣ በስነ ልቦና፣ በእርግዝናና በጤንነት ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለምና ችላ ማለትን አስወግደን ጥንዶች እርስ በርስ በመተሳሰብ አንዳችን ለሌላችን የደስታ፣ የሳቅ፣ የጤነኛ ስሜት ምክንያት ለመሆን ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። ጥንዶች ጉዳዩ ከቁጥጥራችንና ከአቅማችን ውጭ ካልሆነብን በስተቀር ለትዳር አጋሮቻችን የመጥፎ ስሜት መፈጠር ምክንያት እንዳንሆን ለስሜታቸው በመጠንቀቅ የእውነተኛ አፍቃሪ ባልና ሚስት ባህርይ መገኛዎች ልንሆን ይገባናል።

## 5. የባሕርይ ለውጥ

የሰው ባሕርይ አብሮት በሚኖረው ሰው፣ በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በሚኖርበት አካባቢና ሁኔታ ሊቀረጽና ሊለወጥ ይችላል። እውነተኛው ባህሪያችን ሊገለጥ የሚችልበት ቦታ ትዳራችንና ቤተሰባችን ውስጥ ነው። በተለያዩ ነገሮች ተሸፍኖ የነበረው ማንነታችን የምንፈልገውን ስናገኝ ወይም ስናጣ፣ እምነታችንና ዋጋ የምንሰጠው ነገር ዋጋ ሲሰጠው ወይም ዋጋ ሲያጣ እና በተለያዩ ነገሮች ምክንያት ስሜታችን በደስታ ወይም በሐዘን ሲነካ እየተገለጠ መምጣቱ አይቀሬ ነው። አንዳንድ ያልታሰቡ ጉዳዮችና ለውጦችም በባህሪይ ላይ ለውጥ ሊያስከትሉ  ይችላሉ። ወደ ትዳር ከገቡ በኋላ የሚፈጠሩ የባህሪይ ለውጦች ምናልባት ከማግባት በፊት የነበሩ ነገር ግን አንደኛው አካል ራሱን ሁኖ ባለመቅረቡ ምክንያት ተደብቀው የነበሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሌላው ደግሞ ስሜታዊ አፍቃሪ በመሆናቸው ምክንያት የትዳር ጓደኛቸው ባሕርይ አልታይ ብሏቸው ከቆየ በኋላ ወደ ተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች በሚገቡ ወቅት የትዳር አጋራቸውን ባሕርይ አስተውለውት ሊሆን ይችላል።

በወንዶች (ባሎች) ላይ ከሥራ ድካምና ውጥረት የተነሳ፣ የጠበቁት እንዳሰቡት ሳይሆን ሲቀር፣ ወሲባዊ ግንኙነት ሲነፈጉና ሌሎች የተለያዩ ጫናዎች ሲፈጠሩባቸው ወቅታዊ የሆነ የባሕርይ ለውጥ ሊታይባቸው ይችላል። በሴቶች (በሚስቶች) ላይ ደግሞ በወር አበባ፣ በእርግዝና ወቅትና ከወሊድ በኋላ በሚፈጠር ድብርትና ልጆችን በማሳደግ ሂደት ከባል ምንም ዓይነት እርዳታ የማያገኙ ከሆነ በሚፈጠርባቸው የተለየ መጥፎ ስሜት የተለየ የባሕርይ ለውጥ  ሊታይባቸው ይችላል።





## 6. መንፈሳዊ ለውጥ

በጥንዶቹ ሕይወት ከሚፈጠሩ ለውጦች መካከል መጠቀስ ያለበት ሌላው ለውጥ መንፈሳዊ ለውጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን መንፈሳዊ እድገት የማያቋርጥ ማለትም ክርስቶስ በአካል ዳግም እስኪመጣ ወይም ግለሰቡ በግል ወደ ጌታ በስጋው ሞት በማንቀላፋት እስኪጠራ ድረስ የሚቀጥል ሂደት ነው። የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ልኩ ክርስቶስን መምሰል መሆኑ እድገቱ የማያቋርጥ እንዲሆን ያደርገዋል። በዚህ የመንፈሳዊ ብስለትና እድገት ሂደት ውስጥ የጥንዶቹ ሕይወት በተለያዩ ምክንያቶች እድገት ሊያቆም፣ የመንፈሳዊ ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው ግለት እንዲሁም ለጌታና ለቅዱሳን ያላቸው ፍቅር እየቀዘቀዘ ሊመጣ ይችላል።

ከላይ የተጠቀሱ የተለያዩ ለውጦች በጥንዶች በግልና በጋራ የመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እድገትና ብስለት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ሊፈጥሩባቸው ይችላሉ። መንፈሳዊ ለውጥም ሌሎች የተለያዩ ለውጦች እንዲከሰቱ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ መፍጠሩ አጠያያቂ አይደለም። በጥንዶች መካከል የሚፈጠር አለመግባባትና ግጭት በእርግዝናና ልጅ ወልዶ በማሳደግ ሂደት ወቅት ከአሁን በፊት የነበሩ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች እየቀነሱ ብሎም እየጠፉ በመምጣታቸው ምክንያት ሊከሰት ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ወቅት አንዱ የሌላውን መንፈሳዊ እድገት በመረዳት የተለየ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ መጋቢዎች፣ መሪዎች፣ የበሰሉ ሰዎች አገልግሎት የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸትና መንፈሳዊ አቅም ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነው። ምናልባት በአንዱ አካል ላይ ብቻ የሥራ ጫና በዝቶ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጊዜና ፍላጎት ማጣት ሊፈጠር ስለሚችል በቤት ውስጥ ያሉ ሥራዎችን ኃላፊነት መከፋፈል፣ መረዳዳት ብሎም በተራ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ለመካፈል ሁኔታዎችን በግልጥነት በመነጋገር ማመቻቸት የጤናማ ባልና ሚስት ብስለት መለያ ነው፡፡

## 7. ማሕበራዊ ለውጥ

በጥንዶች መካከል አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር ሊያደርጉ ከሚችሉ ለውጦች መካከል መጠቀስ ካለባቸው አንዱ ማሕበራዊ ለውጥ ነው። በተፈጥሮ የሚከሰቱ የተለያዩ ለውጦችና በጥንዶች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በማሕበራዊ ግንኙነታቸው ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ ማምጣታቸው አይቀሬ ነው። የንጥረ ቅመም፣ አካላዊ፣ ስሜታዊና ስነ ልቦናዊ የባህሪይ ለውጦች በማሕበራዊ ሕይወት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ለምሳሌ የሳሙኤል እናት ሀና ልጅ ከመወለዱ በፊት ብቸኛ፣ በትዳሯ ደስተኛ ያልነበረች፣ በጣውንቷ የምትነቀፍ፣ በሊቀ ካህኑ በኤሊ ሰካራም ተብላ የተሰደበች ሴት ነበረች። ከነበረባት አሉታዊ ማሕበራዊ ግንኙነት ነፃ በመውጣትና ከድብርት በመላቀቅ ቀና ብላ ከሌሎች ሰዎች ጋር በነፃነት ኅብረት ማድረግ የጀመረችው ሳሙኤልን ከጸነሰችና ከወለደች በኋላ ነበር /1ኛሳሙ 1፡ 6-2፡ 7/። ይህ ዓይነቱ የማሕበራዊ ለውጥ ሂደት ደግሞ በአንደኛ ሳሙዔል ምዕራፍ አንድ እንደተገለጠው ከባለቤቷ ከህልቃና ጋር በነበራት ግንኙነት ላይም ተጽዕኖውን አሳርፏል፡፡

በሌላው አቅጣጫ ደግሞ ልጅ መውለድና ማሳደግ የሚጠይቀው ኃላፊነት በቤተ ክርስቲያን ከሚደረጉ ኅብረቶችና ከሌሎች ማሕበራዊ ግንኙነቶች በመለየት ብቸኝነት እንዲፈጠር ሊያደርግና ይህ ማሕበራዊ ለውጥ ደግሞ የተለያዩ ተጽዕኖዎች እንዲፈጥሩ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ባልና ሚስት ማሕበራዊ ለውጦችን ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተጽዕኖዎች በመረዳትና ችግሩ ጊዜያዊ መሆኑን በማስተዋል እርስ በርስ መተጋገዝና ነገሮችን ሚዛናዊነትን በጠበቀ ሁኔታ የማስኬድ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ ይህን ማድረጋቸው ለትዳራቸው ጤናማነትም ሆነ ለጠንካራ ቤተሰብ መፈጠር ዓይነተኛ መፍትሔ ነው።

## III. የተለያዩ ወቅታዊ የለውጥ ደረጃዎችና ባሕርያቸው

አንዳንድ የትዳርና የሌሎች ግንኙነት አማካሪዎችና አስተማሪዎች በግንኙነት ሂደት የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉ ይገልጻሉ። እነዚህ የተለያዩ ደረጃዎች ራሱን የቻለ ወቅት፣ ሂደት፣ ባሕርይና ትኩረት እንዳላቸው ይጠቁማሉ። እነዚህን የተለያዩ የግንኙነት ደረጃዎች መረዳት አስቀድሞ ለዝግጅት፣ ወቅቱ ሲመጣ ግጭትን ለመቀነስ፣ ለመቆጣጠርና ከወቅቱ እንድንማር እንጂ እንዳንመረር የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ከዚህ የተነሳ እኔም እነዚህን አምስት የግንኙነት ደረጃዎችን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የትኛው ደረጃ ላይ እንዳለንና እንዴትስ ወደ ሌላው ደረጃ በመልካም ግንኙነት መሸጋገር እንደምንችል አቅጣጫ ለማሳየት በማሰብ ከዚህ በታች ለመዘርዘር እሞክራለሁ፡፡[6]

### 1. የጫጉላ ቤት ጊዜ (የሃኒሙን ወቅት)

የጫጉላ ጊዜ (የሃኒሙን ወቅት) የሚባለው ብዙ አዲስ ተጋቢዎች ጋብቻ ከፈጸሙበት ቀን አንስቶ ለተወሰኑ ቀናት፣ ወራትና ዓመታት የሚያልፉበት ወቅታዊ የመዝናናትና የመደሰት ሂደት ነው። ከላይ ለመግለጥ እንደ ሞከርኩት ይህ የጫጉላ

[6] Gregory A. Kuhlman. Marriage facts. Stages of marriage: http://www.stayhitched.com/stages.htm accessed March 25, 2014.





ወቅት እንደ ባለትዳሮች ሁኔታ ሊወሰን ይችላል። በዚህ የጫጉላ ወቅት ጥንዶች አንዳቸው ለአንዳቸውና በአጠቃላይም ለትዳር ባላቸው ከፍተኛ የሆነ ግምት የሚኖሩበት፣ አብዛኛውን ጊዜ ሰላምና ደስታ የሚታይበት፣ ጠንካራ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚኖርበት፣ ተከታታይነቱ የሚበዛበትና ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥበት ወቅት ነው።

የጫጉላ ቤት ወቅት ጥንዶቹ በጋራ የሚያሳልፉበት፣ አቅማቸው በፈቀደና ከዚያም ባለፈ በብድር የሚዝናኑበት፣ የተለያዩ ቦታዎችን ማለትም ከተሞችን፣ ምግብ ቤቶችን፣ ታላላቅ ሆቴሎችን፣ መዝናኛ ቦታዎችን በመዘዋወር የሚጎበኙበትና በመዝናኛ ስፍራዎች የሚያሳልፉበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት አንዱ ሌላውን ለማወቅ ጥረት የሚያደርጉበትና ያላቸውን አንዱ ለሌላው የሚያካፉሉበት ወቅት ነው። ይህን ወቅት አቅምና ጊዜ በፈቀደ መጠን በጋራ በመደሰትና ግንኙነትን በማጠናከር ማሳለፍ ተገቢ ነው። ነገር ግን የጫጉላ ሽርሽር መደበኛ የተጋቢዎች ኑሮ አይደለም፡፡ ስለዚህ ጥንዶች እውነታውን በመረዳት ትዳር ሁልጊዜ እንዲህ ሁኖ ሊቀጥል እንደማይችል፣ ሌላ ወቅት እንደሚመጣና ይህ የሽግግር ወቅት በግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማምጣት የነበሩትን መልካም ቀናት ሁሉ አስረስቶ ድንጋጤ እንዳይፈጥር እንዲሁም ለግጭትና ከትዳር ሕይወት ለመውጣት ሰበብ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### 2. ከእውነታ ጋር የሚጋፈጡበት ወቅት

ይህ የጋብቻ ወቅት አዲስ ባለትዳሮች ከአሁን በፊት በእጮኝነትና በተጋቡ በተወሰኑ ወራት ወይም ዓመታት ገጥሟቸው የማያውቅ ሁኔታ ጋር ሊጋፈጡ የሚችሉበት ወቅት ነው። አስቀድሞ በእጮኝነት ጊዜ የነበረው ግንኙነት አጭርና ገደብ ባለው ሁኔታ የተያዘ ስለነበር ይበልጥ በጥንቃቄና አንዱ ሌላውን ላለማጣት በሚፈጠር የውስጥ ፍርሃት የማስመሰልና የማመቻመች አዝማሚያ የሚታይበት ሆኖ አልፎ ሊሆን ይችላል። እውነታው ግን ጥንዶቹ በዚህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ የሚቀጥሉ አለመሆናቸው ነው፡፡ እንዲህ ታፍኖ የቆየውና ነፃ ባልሆነ ግንኙነት ላይ የተመሠረተው የማስመሰል፣ የማመቻመችና በፍርሃት የመጠባበቅ መሠረት ላይ በጋራ ዓለምን የመቅጨቱ የወረት ጊዜ ያልፋል፡፡

ጥንዶቹ በሕይወታቸው ከተለያዩ ተፈጥሯዊና የተጠበቁም ሆነ ያልተጠበቁ የሕይወት ገጠመኞችና ችግሮች ጋር በሚጋፈጡበት ወቅት የማስመሰል ጭምብላቸው ተገፍፎ ራሳቸውን መሆን ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በሕይወታቸው በሚገጥሟቸው ተግዳሮቶችና በሚጋፈጧቸው የተለያዩ እውነታዎች ሰበብ ያልለመዱት አለመስማማት ከዚያም አልፎ ብዙ ግጭቶች በግንኙነታቸው ሊፈጠሩባቸው ይችላሉ። በተፈጠረው ግጭት ምክንያት የተለያዩ አንዳንድ ባዕድ የሆኑ ስሜቶች ይፈራረቁባቸዋል። በሚፈጠሩ ያለመግባባትና የግጭት መንስኤዎችና ባሕርያት አንዱ በሌላው የመደናገጥ፣ የማዘን፣

ከፍተኛ የሆነ ተስፋ የመቁረጥና የወደ ፊት የትዳራቸውን ጉዞ ሲያስቡም የፍርሃት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል።

በተፈራረቀባቸው የተለያዩ የለውጥ ስሜቶች ምክንያት በትዳር ጓደኛ ምርጫ ውሳኔያቸው እንደተሳሳቱና ትክክል እንዳልነበሩ ሊሰማቸውና ሊጸጸቱ ይችላሉ፡፡ ከትዳር አጋራቸው ጋርም አብረው ሊሄዱ የማይችሉ እንደሆኑ ያስባሉ። በብዙ ፀፀትና ምሬት ውስጥ በመሆን ደስታ ሊርቃቸው፣ ምሬትና ማጉረምረም ብሎም አንዱ በሌላው ላይ በማሳበብ መነጫነጭና መቆጣት፣ የትዳር ጓደኛቸውን ወይም ራሳቸውን ያለአግባብ ጥፋተኛ የማድረግ ስሜት ሊፈራረቅባቸውና ይበልጥ ግጭታቸውን ሊያባብስባቸው ይችላል።

በመካከላቸው በተከሰቱ አዳዲስ ሁኔታዎች የተፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች አይቀሬነት ተፈጥሯዊና በማንኛውም ባለትዳር መካከል ሊፈጠር የሚችል ስለማይመስላቸው ራሳቸውን ብቻ እየኮነኑና በእነርሱ ላይ ብቻ የተፈጠረ አድርገው በመቁጠር ይበልጥ ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ በሚያልፉበት ግጭትና ጥፋትም የሚሸማቀቁበትና የሚያፍሩበት ጊዜ ይኖራል። በመካከላቸው የተፈጠረው አለመግባባትና ግጭትም ሊፈታ የማይችልና መፍትሔ የሌለው እንደሆነ እያሰቡ ብቻቸውን ይሰቃያሉ።

ባለትዳሮች በዚህ ወቅት እንዲህ ዓይነቱን እውነታ በብስለትና በተዘጋጀ ማንነት ለመጋፈጥ እንዲሁም የማይፈልጓቸው የተለያዩ ስሜቶች ሲፈራረቁባቸውና በውሳኔ እንደተሳሳቱ የመቁጠር ስሜት ሲሰማቸው የትዳር ግንኙነታቸው እንዳይሻክር ወቅቱን በማስተዋል፣ በመረዳዳትና በመግባባት ለማለፍ ነገሮችን በሰከነ መንፈስ የሚመዝን ጠቢብነትና ሁኔታን ታግሶ የሚያልፍ የፍቅር ሕብረት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ግጭት በማንኛውም የጋብቻ ዘመን አይቀሬ እንደ ሆነ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ወቅት ሌሎች እንዴት እንዳለፉ በመማርና ልምድ በመውሰድ ተደጋግፎ ለማለፍ እንጂ በዛሬው ችግር አሉታዊ ተጽዕኖ ነገን አብረው እንዳያዩ በሚከለክል መጋረጃ ተሸፍነው ተስፋ እንደሌለ እንዳያስቡ ጨለምተኝነትም እንዳይሰማቸው ከወዲሁ በእውቀት መዘጋጀት ተገቢ ነው።

## 3. በልጆች ላይ ትኩረት የሚወስዱበት ወቅት

ይህ ሶስተኛው የትዳር ደረጃ ጥንዶች ልጅ በመውለድ የቤተሰብ አባላትን የሚጨምሩበትና አዲስ ልምምድ ውስጥ የሚገቡበት ወቅት ነው። ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው ነገር ግን ልጆች ስጦታዎች ብቻ ሳይሆኑ ኃላፊነትም ጭምር መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። ልጆችን ማሳደግ ራሱን የቻለ የተለየ ልምምድ ነው። ልጅ የመውለድና የማሳደግ ልምምድ ጥንዶች ቀድሞ የነበራቸውን የትኩረት አቅጣጫ ሊቀይርና በመካከላቸው የኑሮና የግንኙነት ውጥረት እንዲጨምር ምክንያት ሊሆን የሚችል ልምምድ ነው።





ይህ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያጋጥም ባለትዳሮች ቀድሞ ከነበሯቸው ኃላፊነቶች በተጨማሪ የተለያየ ሥራ፣ ጊዜና ጉልበት የሚጠይቅ በመሆኑ ኃላፊነቱን በተግባር ለመወጣትና ልጅን ለማሳደግ ጥንዶቹ ልምድ ከሌላቸው በመካከላቸው ውጥረት እንዲፈጠርና ግጭት እንዲባባስ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ሂደት ካለፈው በመማርና ብስለትን በማሳደግ ካልተያዘ ሁለተኛና ሶስተኛ ልጅ በሚወለድበት ወቅት ውጥረቱ ይበልጥ ይጨምራል፡፡ ጥንዶች የራሳቸው ጊዜ እንዳይኖራቸው፣ ግንኙነታቸው ላይ ትኩረት እንዳያደርጉና ወደ ልጆቻቸው እንዲያዘነብሉም ያስገድዳቸዋል። ይህን በመረዳት በዚህ ወቅት ትዳር ላይ ችግር እንዳይፈጠር ለየት ያለ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባዋል።

ልጆች በሚወለዱበት ወቅት የወላጆች ትኩረት ልጆች ላይ መሆኑ ፍቅር እንደቀዘቀዘ ወይም እንደጠፋና የትዳር ግንኙነት እንደ ተቋረጠ አድረጎ በማሰብ ባል ወይም ሚስት ፍርሃትና ድንጋጤ ውስጥ እንዳይገቡ ከወዲሁ ጉዳዩ ሊከሰት የሚችል መሆኑን ሊረዱ ይገባል። የእግዚአብሔር ስጦታ የሆኑት ልጆች በባለትዳሮች መካከል ገብተው የትዳር ግንኙነት መሠረት የሆነው ፍቅር ለመቀዝቀዙና ለመጥፋቱ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ እንዳይፈጠር ጥንዶች ሁኔታዎችን በማመቻቸት አብረው ጊዜ በማሳለፍ ግንኙነትን ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት ሊያደረጉ ይገባል። ነገ ልጆች አድገውና ለቁም ነገር ደርሰው ቤታችንን ለቀው የሚወጡበትና ራሳቸውን የሚችሉበት ወቅት እንደሚመጣ በማሰብ ወላጆች ለግንኙነታችን ለየት ያለ ትኩረት መስጠት ያሻናል። በእርግጥ ልጆችን ማሳደግ ኃላፊነት ቢሆንም ከትዳር አጋር ግን ልናስበልጣቸውና ልናስቀድማቸው አይገባም። ለልጆች መገኘት ምክንያት የሆነው የጋብቻ ተቋምም በልጆች መወለድ ምክንያት ቀውስ ውስጥ መግባትም ይሁን መፍረስ የለበትም፡፡ ልጆች የወላጆች ኃላፊነትና ደስታ ናቸውና የልጆች መወለድ የባልና የሚስትን ግንኙነት የበለጠ የሚያጠናክርና ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ የሚያግዝ ጠቃሚ ግብዓት በመሆን እንዲያገለግል ወላጆች በብስለት፣ በእውቀትና በተረጋጋ ማንነት ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

**የሚሰጡን ማንኛውም ስጦዎች ሁሉ ይብዛም ይነስም ኃላፊነት እንዳላቸው መዘንጋት የለብንም!!**

## 4. የትዳርን ግንኙነት ለማደስ ጥረት የሚደረግበት ወቅት

የትዳር ግንኙነትን የማደስ ጥረት የሚጌጉላ ዘመንን በማስታወስ፣ የኑሮ እውነታዎችን በመጋፈጥና ትኩረታቸውን በልጆች ላይ በማድረግ የተለያዩ ደረጃዎችን ያሳለፉ ጥንዶች የጋራ የትዳር ግንኙነታቸውን ለማደስ የሚነሱበትና የሚንቀሳቀሱበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት አንዱ ሌላውን እንደሚገባ የሚያወቁበት፣ ምን እነደሚያስፈልጋቸው የሚረዱበት፣ ልዩነታቸውን የሚያጠቡበት፣ አለመግባባትንና

ግጭትን የሚቆጣጠሩብት እንዲሁም የሚያስተካክሉበት ወቅት ነው። ይህ ደረጃ ካለፈው ስህተታቸው በመማር ለዛሬና ለወደፊት ትዳራቸው የሚያስቡበት፣ በጋራ በመረዳዳት እንዲሁም አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ በግንኙነታቸው ይበልጥ ደስ እየተሰኙ የሚኖሩበት ደረጃ ነው። ይህ ደረጃ ብዙ ያስጨነቋቸውን፣ ያሳዘኗቸውንና  ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ እንዲፈራረቅባቸው ያደረጓቸውን ሁኔታዎች ጥሩ ትምህርት ቤት አድርገው በማየት ባለፈው አስቸጋሪ ዘመን ተምረውበት ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩበት ለአዲስ ኅብረት፣ ፍቅርና አብሮነት የሚታደሱበት ደረጃ ነው። ጥንዶች ነገሮች ሁሉ እንዲህ እንደሚያልፉና ዛሬን መድረስ ብሎም ነገን በተሻለ መንገድ መገናኘት እንደሚቻል አምነውና ተቀብለው እንዲቀጥሉ ሊበረታቱ የሚችሉበት አድርገው ከተጠቀሙበት ከዚህ ወርቃማ ሂደት ብዙ ያተርፉበታል።

## 5. በትዳር ግንኙነት ውጤታማ የሚሆኑበት ወቅት

የመጨረሻው የትዳር የግንኙነት ደረጃ የጋብቻን ዓላማና ጥቅም በመረዳትና አንዱ የሌላውን ፍላጎት ይበልጥ በማሟላት በግንኙነታቸው በጣም ደስተኛ የሚሆኑበት ወቅት ነው። ይህ ደረጃ ለብዙ ዓመታት ካሳለፉት የሕይወት ውጣ ውረድ የተማሩትን፣ በብዙ ሁኔታዎች የተፈተነ ማንነታቸውንና ግንኙነታቸውን ይበልጥ እያደነቁና እያከበሩ የሚይዙበት የትዳር ደረጃ ነው። ይህ ደረጃ ባልና ሚስት እርስ በርስ እየተዋደዱ፣ እየተከባበሩና እየተረዳዱ ለመኖር ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉበት ደረጃ ከመሆኑ የተነሳ ወደ ፊት ስጋት ሳይሆን ተስፋ፣ ሽንፈት ሳይሆን ድል፣ በግጭት መደናገጥ ሳይሆን ተረጋግቶ ችግርን መፍታት ይታያቸዋል፡፡ ይህ ወቅት በሚያልፉት አስቸጋሪ ሁኔታ ተመራሪነትን ሳይሆን ተማሪነትን፣ ግለኝነትን ሳይሆን አብሮነትን እንዲሁም ተጠቃሚነትን ብቻ ሳይሆን ጠቃሚነትን ለመምረጥ ዝግጁ የሚሆኑበት ወቅት ነው።

ይህ ማለት በዚህ ወቅት አለመግባባትና ግጭት የለም ማለት አይደለም። ነገር ግን ለግጭት መነሻ የሚሆኑ ምክንያቶችንና ግጭቶችን የሚፈቱበትን መንገድ ከቀደሞው በተለየና በበሰለ ማንነት የሚይዙበት ወይም የሚያስተናግዱበት ጊዜ ነው። በዚህ የጋብቻ ደረጃ ላይ ያሉ ጥንዶች ሌላው አስቸጋሪ ጊዜ የሚሆንባቸው ልጆቻቸው 16 ዓመት ላይ የሚደርሱበት ወቅት ነው። ይህ ራሱን የቻለ ለትዳርና ለቤተሰብ ግንኙነት አስቸጋሪና ፈታኝ ሊሆን የሚችልበት ጊዜ ሲሆን የትዳር ሕይወት መመረቅ የሌለበት ትምህርት ቤት መሆኑንም ያሳያል። ለቤተ ክርስቲያን መሪነት የሚታጭ አማኝ እንኳን ቤቱን በመልካም የሚያስተዳድር መሆኑ የሚጠየቀውና በዚህ መርህ የማስተዳደር ማንነቱ በቤቱ መፈተን አለበት የሚባለው እንደዚህ ዓይነቱን ተግዳሮት በአግባቡ መወጣት የሚያስችል በሳል የቤት አስተዳደር ጥበብ ወይም ክህሎት ያለው መሆኑን ይህ ወቅት ስለሚያሳይ ነው። *"ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤት ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?"* /1ኛጢሞ 3፡ 5-6/፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ በመልካም ሁኔታ የደረሱ ባለትዳሮች በአመታት የትዳር የአብሮነት ጉዞ በተገኘው የተሳካ የግንኙነት ብዙ ውጤትና ፍሬያማነት መደሰትና መርካት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ወቅትም እንኳን በትዳር ሕይወት ውስጥ ተማሪዎችና ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች መሆናቸውን በመረዳት የተገነባው የጋብቻ ሕይወት ስኬት የበለጠ እየታነፀ እንዲቀጥል የሚያግዝ ገንቢ አስተዋፅዖቸውን ማበርከት አለባቸው፡፡

**ባለትዳሮች ሆይ በምናልፉብት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ተመራሪነትን ሳይሆን ተማሪነትን፣ ግለኝነትን ሳይሆን አብሮነትን እንዲሁም ተጠቃሚነትን ብቻ ሳይሆን ጠቃሚነትን ለመምረጥ ዝግጁ ልሆን ይገባል።**



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!